# የቤተ ክርስቲያን

# ተልእኮ

ከዶር ኃይሌ ወ/ሚካኤል

ይህንን መጽሐፍ ያለ ደራሲው ፈቃድ ማባዛት

ወይም ማሳተም የተከለከለ ነው ።

DALLAS, TX 75218

# የቤተ ክርስቲያን

# ተልእኮ

ከዶክተር ኃይሌ ወ/ሚካኤል

P.O.Box 306
PASADENA CA 91102
USA

Printed in USA

June 1994



ETH... DALLAS, TX 75213

# ምስጋና

1/ ከብዙ ምህረቱና ከታላቅ ፍቅሩ የተነሳ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ያዳነኝንና የዘላለም ሕይወት የሰጠኝን ፥

2/ ለውድ ልጁ ለኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል አገልግሎት የጠራኝን ፥

3/ እስከ ዛሬ ድረስ በሕይወትም በአገልግሎትም የረዳኝን እግዚአብሔር አምላኬን ከልብ አመሰግናለሁ ።

4/ ስለ ሕይወቴም ሆነ ስለ አገልግሎቴ ለሚጸልዩልኝ ፥ እንዲሁም እግዚአብሔር እንዳሳሰባቸው ይህን አገልግሎት በገንዘብ ለሚደግፉ ሁሉ " እግዚአብሔር አብዝቶ ይባርካችሁ " እላለሁ ።

እንዲሁም ይህን መጽሐፍ በፍቅር መንፈስ በኮምፒዩተር የቀረጹልኝን አቶ ድንቁ ጃለታንና ባለቤቱን ወ/ሮ ሰብለ በጋሻዉን በጌታችን ስም ከልብ አመሰግናለሁ።

# መግቢያ

በዘመናችን ያሉትን የአንዳንድ ቤተ ክርስቲያኖች ሕይወትና ትምህርት ስንመለከት ግራ እንጋባለን ። “ለመሆኑ የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ተልእኮ ምንድነው ?” ብለን ራሳችንን እንድንጠይቅ እንገደዳለን ።

እነዚህ ቤተ ክርስቲያኖች ለምን እንደሚኖሩ የሚያውቁ አይመስሉም ። ራእይ የሌላቸው ፥ በየጊዜው እንደ ነፋስ የሚነፍሰውን የዘመኑን ፍልስፍና የሚከተሉ ናቸው ። የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ ምን እንደሆነ የሚያውቁ አይመስሉም ።

የእግዚአብሔርን ቃል መሠረት አድርገው ጌታን ለማገልገል የሚፈልጉ ወንጌላውያን ቤተ ክርስቲያኖችም እንኳ አንዳንድ ጊዜ የቤተ ክርስቲያንን ተልእኮ ጥርት አድርገው ካለመረዳት የተነሳ ቅድሚያ መስጠት የሚገባቸው አገልግሎቶች አስፈላጊውን ቅድሚያ ሳይሰጡዋቸው እንዲያው በሌሎች ተራ ጉዳዮች ላይ ይባክናሉ ።

የቤተ ክርስቲያንን ተልእኮ ጥርት ባለ ሁኔታ ማወቅ ጊዜንም ፥ ገንዘብንም ፥ አገልጋዮችንም በማስተዋል አስፈላጊ በሆኑት የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች ላይ ለማዋል ይረዳል ። ቤተ



ክርስቲያን ተልእኮዋን ካላወቀች እንዲያው ካልተላከችበት በማይመለከታት መስክ ውስጥ በከንቱ ስትኳትን ትኖራለች ።

በዚህ በጻፍሁበት ርዕስ ፥ የልዩ ልዩ ሊቃውንትን መጻሕፍት በመጥቀስና ልዩ ልዩ አመለካከቶችን በማተት ፥ ተለቅ ያለ መጽሐፍ ለመጻፍ እችል ነበር ። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስን ብቻ መሠረት በማድረግ ፤ አጠር አድርጌ ፍሬ ነገሮችን ማቅረብ የበለጠ ጠቃሚ ስለመሰለኝ አሁን ለጊዜው በዚህ መልክ አዘጋጅቻለሁ ። ይህንንም ዘዴ የመረጥኩበት ምክንያት ምንም ዓይነት የትምህርት ደረጃ ያለው አማኝ መጽሐፉን አንብቦና አሳቡን ተረድቶ ለመጠቀም እንዲችል ነው ።

ይህን መጽሐፍ በሶስት መንገዶች ጥቅም ላይ ለማዋል ይቻላል

1ኛ/ መጽሐፉን በግለሰብ ደረጃ በማንበብና በማጥናት በውስጡ በሰፈሩት ፍሬ ነገሮች የግልን ሕይወትና አገልግሎት ማሳደግ ።

2ኛ/ በመጽሐፉ ውስጥ የሰፈሩትን ፍሬ ነገሮች በሕብረት በማጥናት ለመንፈሳዊ ሕይወትና አገልግሎት እድገት ማዋል ።

3ኛ/ እንዲሁም በመጽሐፉ ውስጥ የሰፈሩትን መሠረታዊ አሳቦች ወስዶና ካስፈለገም አዳብሮ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አገልጋዮችን ማሰልጠን ።

የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ (ቆላ 1:18) ይህን መጽሐፍ ለወንጌሉ መስፋፊያ እንዲያደርገው ጸሎቴ ነው ።



# ማውጫ


መግቢያ ........................................ 4

ምዕራፍ 1 ........................................ 8

የተልእኮ እቅድ

ምዕራፍ 2 ........................................ 13

የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ በስእላዊ መልክ

ምዕራፍ 3 ........................................ 16

ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር መመለስ

ምዕራፍ 4 ........................................ 29

ቤተ ክርስቲያን በቁጥር የምታድግበት ዘዴ

ምዕራፍ 5 ........................................ 64

የምእመናንን መንፈሳዊ ሕይወት ማነጽ

ምዕራፍ 6 ........................................ 84

ምእመናንን ለመንፈሳዊ አገልግሎት ማዘጋጀትና ማሰለፍ

ምዕራፍ 7 ........................................ 93

እግዚአብሔርን በእውነትና በመንፈስ ማምለክ

ምዕራፍ 8 ........................................ 103

ችግረኞችን መርዳት

ምዕራፍ 9 ........................................ 108

በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ መድረክ

መደምደሚያ ........................................ 136

# ምዕራፍ 1

## የተልእኮ እቅድ

የተልእኮ አሳብ በእግዚአብሔር አእምሮ ውስጥ ያልነበረበት ጊዜ የለም ። እግዚአብሔር አብርሃምን የጠራው ከሌሎች ሰዎች የተለየ ስለ ነበረ አይደለም ። ነገር ግን በረከቱን በአብርሃም በኩል ለሌሎች ለማዳረስ ነበር ። እግዚአብሔር አብርሃምን ሲጠራው ይህን አሳብ ግልጥ አድርጎለት እንዲህ ሲል ተናገረው "የምድር ነገዶች ሁሉ ባንተ ይባረካሉ " (ዘፍ 12:3) ።

ነገር ግን አብርሃም ከዚህ በላይ በተጠቀሰው አረፍተ ነገር ውስጥ ያለውን የተልእኮ ምሥጢር ስላልተገነዘበ ተልእኮውን እንደሚገባ አላከናወነም ።

ቀጥሎም እግዚአብሔር የእሥራኤልን ሕዝብ ለራሱ ሲለየው የተልእኮን አሳብ በአእምሮ ይዞ ነበር ። የእሥራኤል ሕዝብ ከሌሎች ሕዝቦች የተለየ ሕዝብ በመሆኑ አይደለም ። ነገር ግን በዚህ ሕዝብ አማካይነት ሌሎችን ሕዝቦች በምህረቱ ለመድረስ ስለፈለገ የእሥራኤል ሕዝብ ለርሱ ምስክሮች ወይም መልክተኞቹ እንዲሆኑ ነበር ።

እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ ሆኖ የእሥራኤልን ሕዝብ ተልእኮ እንዲህ ሲል ተናገረው ፤

"አሁንም እነሆ ለእኔ ብትታዘዙና ቃል ኪዳኔንም ብትጠብቁ



ለእኔ የተለያችሁ ሕዝብ ትሆናላችሁ ፤ ምንም እንኳ ምድር ሁሉ የእኔ ብትሆንም እናንተ ለእኔ የተመረጣችሁና ለእኔም ብቻ የተለያችሁ ቅዱሳን ሕዝብ ትሆናላችሁ፤ እንደ ካህናትም ሆናችሁ ታገለግሉኛላችሁ ፤ ለእሥራኤላውያንም የምትነግራቸው ቃል ይኸው ነው " (ዘጻ 19:5-6) ።

እንደገና ከብዙ ዓመታት በኋላ ስለዚህ ተልእኮ ሲያሳስባቸው እግዚአብሔር እንዲህ ሲል ተናገራቸው ፤

"ለአንተ ለአገልጋዬ [ለእሥራኤል ሕዝብ] ያዘጋጀሁልህ ታላቅ ሥራ አለ ፣ ይኸውም ከጥፋት ለተረፉት የእሥራኤል ሕዝብ እንደገና የታላቅነትን ክብር መስጠት ብቻ አይደለም ፣ ነገር ግን ዓለሙ በመላው ይድን ዘንድ ለአሕዛብ ሁሉ ብርሃን አድርጌሃለሁ " (ኢሳ 49:6) ።

እግዚአብሔር እንደፈለገው የእሥራኤል ሕዝብ የእግዚአብሔር የምህረት መልእክተኞች አልሆኑም ። እግዚአብሔር ሌሎችን ሕዝቦች እንደማይፈልጋቸውና እነርሱ ብቻ የእግዚአብሔር ሕዝቦች እንደሆኑ አሰቡ ። እስራኤላውያን እግዚአብሔርም የእነርሱ ብቻ አምላክ የሆነ መሰላቸው ። ስለዚህ የእግዚአብሔርን የምህረት መልእክት ለሌሎች ለማስተላለፍ ፣ ለማዳረስ አልሞከሩም ።

እግዚአብሔር ይህን የምህረት ዜና ለሌሎች ሕዝቦች ለማስተላለፍ ፍቃደኛ ያለመሆናቸውን በግልጥ የምንረዳው በትንቢተ ዮናስ ውስጥ ነው ።

1/ የእግዚአብሔር ሕዝብ የእሥራኤልን ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም ሕዝቦች ይወዳል ።

2ኛ/ የእሥራኤል ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ሕዝቦች በንስሐ ወደ እርሱ እንዲመለሱ ይፈልጋል ።

3ኛ/ የእሥራኤል ሕዝብ ነቢዩም ሳይቀር የእግዚአብሔር የይቅርታ መልእክት ከእሥራኤል ሕዝብ አልፎ ለሌሎችም ሕዝቦች እንዲዳረስ አልፈለጉም ።

4ኛ/ በተላኩም ጊዜ ለንስሐ የሚጠራውን መልእክት ለሌሎችም ሕዝቦች ለማዳረስ አልፈለጉም ።

ከዚህ የተነሳ እግዚአብሔር ቀደም ብሎ በአብርሃም አማካይነት ቀጥሎም በእሥራኤል ሕዝብ በኩል ለሌሎችም የዓለም ሕዝቦች እንዲደርስ የፈለገው የምህረት አዋጅ ሳይደርስ ቀረ ።

ይሁን እንጂ እግዚአብሔር የተልእኮ ዓላማውን አልሰረዘም ። ጊዜውን ጠብቆ (ገላ 4:4) በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የፍቅሩና የምህረቱ ታላቅነት ለዓለም ሕዝቦች ሁሉ እንዲደርስ ወሰነ ።

ከአይሁድ ወገን የሆኑ ክርስቲያኖች እንኳ ሳይቀሩ የእግዚአብሔር ፍቅር ፣ ምህረትና በረከት ከእሥራኤል ሕዝብ አልፎ ለሌሎች ሕዝቦች የሚገባ መስሎ አልታያቸውም ነበር ። ለምሳሌ ከአሕዛብ ወገን የሆኑት ቆርኖሌዎስ ፣ ቤተሰቡና ጓደኞቹ የእግዚአብሔርን ምህረትና ፍቅር ተቀብለው በመንፈስ ቅዱስ በተሞሉ ጊዜ ከአይሁድ ወገን የሆኑ ክርስቲያኖች ተደነቁ ።



"ጴጥሮስ ይህንን ነገር ሲናገር ቃሉን በሰሙት ሁሉ ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው ከጴጥሮስም ጋር የመጡት ሁሉ ከተገረዙት ወገን የሆኑ ምእመናን በአሕዛብ ላይ ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ስለ ፈሰሰ ተገረሙ " (የሐ. ሥ 10:44-45) ።

ለምን ተገረሙ ? እግዚአብሔር ከእሥራኤል ሕዝብ በቀር ሌላ ሕዝብ የሚወድ ፣ የሚምርና የሚባርክ አይመስላቸውም ነበር ። የእግዚአብሔርን ተልእኮ እቅድ በሚገባ ለመረዳት ብዙ ጊዜ ወሰደባቸው ።

ሐዋርያው ጴጥሮስም እንኳ ለመጀመሪያ ጊዜ የእግዚአብሔርን የተልእኮ እቅድ በሚገባ መረዳቱን እንዲህ ሲል ተናገረ :-"በእውነት እግዚአብሔር ሰውን ከሰው እንደማያበላልጥና እንደማያዳላ አስተዋልሁ " (የሐ.ሥ 10:34) ።

ጴጥሮስ ወደ ወገኖቹ በመመለስ እግዚአብሔር አህዛብንም እንደሚወድና እንደሚቀበል ባስረዳቸውና የእግዚአብሔርን የተልእኮ እቅድ በተገነዘቡ ጊዜ " እንግዲህ እግዚአብሔር አረማውያንንም ለአዲስ ሕይወት የሚያበቃቸውን ንስሐ ሰጥቶአቸዋል በማለት እግዚአብሔርን አመሰገኑ " (የሐ.ሥ 11:18) ።

አብርሃም ለእግዚአብሔር ተልእኮ ከተጠራበት ጊዜ ጀምሮ ይህን ከዚህ በላይ በሐ.ሥ 11:18 የተናገሩትን የተልእኮ ግንዛቤ እስኪገነዘቡ ድረስ ብዙ መቶ ዓመታት አለፉ ። እግዚአብሔር ቀደም ብሎ በአብርሃም አማካይነት በኋላም በእሥራኤል ሕዝብ በኩል ለዓለም ሕዝብ ለማስተላለፍ የፈለገው የምህረት አዋጅ እንደታቀደው ከግቡ አልደረሰም ነበር ።

ስለዚህ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ልዩ ሕዝብ (ቤተ ክርስቲያን) ለራሱ ከዋጀ በኋላ ይህን ለራሱ የተቀደሰ ሕዝብ አድርጎ የዋጀውን ሕዝብ መልእክተኛው አድርጎ ወደ ዓለም ሕዝቦች ሁሉ ለመላክ ወሰነ ።

እግዚአብሔር ስለዚህ ሕዝብ /ቤተ ክርስቲያንና ስለ ተልእኮው እንዲህ ሲል ተናገረ ፤

"እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእግዚአብሔርን አስደናቂ ሥራ እንድታውጁ የተመረጠ ትውልድ ፥ የንጉሥ ካህናት ፥ እግዚአብሔር ለራሱ ያደረጋችሁ ቅዱስ ሕዝብ ናችሁ " (1ጴጥ 2:9) ።

ይህንን ተልእኮ ነው የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ ብለን የምንጠራው ። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ስለ ቤተ ክርስቲያን ተልእኮ የማቀርበው አሳብ ኮተት የለበትም ። አላማዬ ስለ ቤተ ክርስቲያን ተልእኮ "እጥርና " "ምጥን " አድርጌ ጥርት ባለ ሁኔታ መሠረታዊ አሳቦችን ብቻ ለማቅረብ ነው ።



# ምዕራፍ 2

## የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ በስእላዊ መልክ

የቤተ ክርስቲያንን ተልእኮ በስእላዊ መልክ ከማስቀመጤ በፊት አራት መሰረታዊ አሳቦችን አሰፍራለሁ ። እነዚህ መሰረታዊ አሳቦች የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ ዋና ዋና ክፍሎች ናቸው ።

ሀ/ ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር መመለስ


ለ/ የምእመናንን መንፈሳዊ ሕይወት ማነጽ

ሐ/ ምእመናንን ለመንፈሳዊ አገልግሎት ማዘጋጀትና ማሰለፍ

መ/ ሕያው እግዚአብሔርን በእውነትና በመንፈስ ማምለክ

እነዚህን ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን መሰረታዊ አሳቦች ከዚህ ቀጥሎ ባለው ስእላዊ መልክ ለመግለጥ ይቻላል ።

# ስእላዊ መግለጫ






ከዚህ በላይ በስእላዊ መልክ ያሰፈርሁአቸው አራት መሠረታዊ አሳቦች የቤተ ክርስቲያንን ተልእኮ ግልጥ ባለ ሁኔታ ያሳያሉ።

ከዚህ ቀጥሎ እነዚህን አራት መሠረታዊ አሳቦች በቅደም ተከተል እንመለከታለን ።

# ምዕራፍ 3

# ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር መመለስ

የቤተ ክርስቲያን የተልእኮ አሳብ የመነጨው ከሕያው እግዚአብሔር ነው ። ስለዚህ ጉዳይ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአራቱ ወንጌላትና በሐዋርያት ሥራ ያዘዘውን የተልእኮ ትእዛዝ መመልከት ይኖርብናል።

እነዚህን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ስንመለከት ጌታችን ኢየሱስ ትእዛዙን ለተከታዮቹ የሰጠው የሶስት አመት የምድር አገልግሎቱን አጠናቅቆ ወደ አብ ከመሄዱ በፊት ጥቂት ጊዜ ሲቀረው መሆኑን መገንዘብ አለብን ። በተጨማሪም ይህ የተልእኮ ትእዛዝ የተሰጠው በአራቱም ወንጌላት መጨረሻ ላይ በሐዋርያት ሥራ መጀመሪያ ላይ መሆኑን ማስተዋል ይጠቅመናል ።

## በአራቱም ወንጌላት መጨረሻ ላይ:-

የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ በአራቱም ወንጌላት በመጨረሻ ላይ መጠቀሱ ምን ቁም ነገር አለው ?

1ኛ/ ጌታችን ኢየሱስ በዚህ ምድር በነበረ ጊዜ እርሱ ያከናውን



የነበረውን ሐላፊነት ለደቀመዛሙርቱ ማስተላለፉን ያመለክታል ። በዮሐ 20:21 " አብ እኔን እንደ ላከኝ እኔም እናንተን እልካችኋለሁ" ሲል ተናገረ ።

2ኛ/ የተልእኮ አጀንዳ የሶስት ዓመት አጀንዳ ሳይሆን ጌታችን ኢየሱስ ተመልሶ እስከሚመጣበት ጊዜ ድረስ የማይለወጥ የቤተ ክርስቲያን አጀንዳ መሆኑን ያሳያል ። ሐዋርያት የዓለምን ሕዝብ ደቀመዛሙርት እንዲያደርጉአቸው ካዘዘ በኋላ " እነሆ እኔ እስከ ዓለም መጨረሻ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ " ሲል ቃል ገባ (ማቴ 28:20) ።

## በሐዋርያት ሥራ መጀመርያ ላይ :-

የተልእኮ ትእዛዝ በሐዋርያት ሥራ በመጀመርያ ላይ መጠቀሱስ ምን የተለየ ትርጉም አለዉ ?

1ኛ/ ጌታችን ኢየሱስ ይህን የተልእኮ ትእዛዝ ለመጨረሻ ጊዜ የሰጠው ወደ አብ ሊሄድ ጥቂት ደቂቃዎች ሲቀሩት ነው ። ስለዚህ ይህ የተልእኮ ትእዛዝ የትእዛዛት ሁሉ ትእዛዝና ማሰርያ ፥ መደጋገም ያለበትና የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የልቡ ትርታ መሆኑን ያስገነዝበናል ።

2ኛ/ የሐዋርያት አእምሮ በምድራዊ መንግሥት አሳብ ተይዞ ስለነበረ የምድራዊ መንግሥት አሳብ ከሰማያዊ መንግሥት ተልእኮ ፈቀቅ እንዳያደርጋቸው ፥ ልባቸው እንዳይከፈልና ራእያቸው እንዳይበላሽ ሲያስጠነቅቃቸው ነው (የሐ.ሥ 1:7-8) ።

አሁን ይህን በአራቱም ወንጌላትና በሐዋርያት ሥራ የተጠቀሰውን ትእዛዝ እንመለከታለን ።

**ማቴዎስ** 28:18-20 :-

"ኢየሱስ ወደ እነርሱ ቀረበና እንዲህ አላቸው ፥ ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጥቶኛል ፥ እንግዲህ ሂዱና የዓለምን ሕዝብ ሁሉ አስተምሩ ፥ በአብና ፥ በወልድ ፥ በመንፈስ ቅዱስም ስም አጥምቁአቸው ያዘዝሁአችሁንም ሁሉ እንዲፈጽሙ አድርጉአቸው እነሆ እኔ ሁል ጊዜ ከናንተ ጋር ነኝ "።

**ማርቆስ** 16:14-16

"ከዚያም በኋላ አሥራ አንዱ በማእድ ቀርበው ሲበሉ ኢየሱስ ታያቸው ፤.... እንዲህም አላቸው ፥ ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ፤ ለሰው ሁሉ ወንጌልን አስተምሩ ። ያመነና የተጠመቀ ይድናል ፤ የማያምን ግን ይፈረድበታል ። "

**ሉቃስ** 24:46-49 :-

"እንዲህም አላቸው ክርስቶስ መከራ እንደሚቀበልና በሶስተኛው ቀን ከሞት እንደሚነሳ አስቀድሞ ተጽፎአል ፥ እንዲሁም በስሙ የንስሐና የኃጢአት ይቅርታ ወንጌል ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በየአገሩ ለሕዝብ ሁሉ እንደሚሰበክ ተናግሮአል ። እናንተም የዚህ ሁሉ ነገር ምስክሮች ናችሁ ፤ እነሆ እኔ የአባቴን የተስፋ ስጦታ እልክላችኋለሁ ፤ እናንተም ኃይል ከላይ እስኪሰጣችሁ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ ።"



**ዮሐንስ** 20:21 :-

"ከዚህ በኋላ ኢየሱስ እንደገና ሰላም ለእናንተ ይሁን ! አብ እንደላከኝ እኔም እናንተን እልካችኋለሁ አላቸው ።"

**የሐዋርያት ሥራ** 1:6-9 :-

"እነርሱም በአንድነት ተሰብስበው ሳሉ ጌታ ሆይ ! መንግሥትን ለእስራኤል መልሰህ የምትሰጥበት ጊዜ አሁን ነውን ? ሲሉ ጠየቁት ። ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው ፥ አብ በገዛ ሥልጣኑ የወሰነውን ጊዜና ዘመን እናንተ ልታውቁት አትችሉም ። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ በኢየሩሳሌም ፥ በይሁዳ አገር ሁሉ ፥ በሰማርያም ፥ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ ። ይህንንም ካለ በኋላ እነርሱ እያዩት ወደ ሰማይ ወጣ ፤ ደመናም ከዓይናቸው ሰወረው ።"

ከዚህ በላይ እነዚህን ጥቅሶች ያሰፈርሁአቸው እንዲሁ ጥቅስ ለማብዛት አይደለም ። ነገር ግን አራቱም የወንጌል ጸሐፊዎችና የሐዋርያትን ሥራ የጻፈው ሉቃስ እንደሰሙትና እንደተገነዘቡት ፥ ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር የመመለስ ጉዳይ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ <u>የልቡ ትርታ</u> መሆኑን በበለጠ እንድንገነዘብ ነው ።

ትእዛዙን ከጌታችን ከኢየሱስ ከተቀበሉት ሐዋርያት አንዱ የሆነው ጴጥሮስ ፥ በጴንጤቆስጤ ቀን የሰበከውን ታላቅ ስብከት እንዲህ ሲል ደመደመው ፤ "እንግዲህ ኃጢአታችሁ እንዲደመሰስላችሁ ንስሐ ገብታችሁ ወደ እግዚአብሔር ተመለሱ " (የሐ.ሥ 3:19)።

ጌታችን ኢየሱስ ወደ አብ ከተመለሰ በኋላ ፥ ጳውሎስን ለወንጌል ሲጠራው የጥሪውን ዓላማ እንዲህ ሲል አስታወቀው ። "....ከሰይጣን ግዛት ወደ እግዚአብሔር እንድትመልሳቸው አደርግሃለሁ ። እነርሱም በእኔ በማመናቸው የኃጢአታቸውን ይቅርታ ያገኛሉ ...." (የሐ.ሥ 26:18) ።

የቤተ ክርስቲያንን የተልእኮ ጥሪ በደማስቆ መንገድ ላይ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የተቀበለው ፥ የተልእኮውን ታላቅነትና ጠባይ በሚገባ የተገነዘበው ጳውሎስ ይህን ተልእኮ እንዴት እንዳካሄደ እንዲህ ሲል ይመሰክራል ፤ "ስለዚህ ንጉሥ አግሪጳ ሆይ ! ከሰማይ ለተሰጠኝ ራእይ ታዛዥ ሆኛለሁ ። ነገር ግን አስቀድሜ በደማስቆ ያሉትን ሰዎች ፥ ቀጥሎም በኢየሩሳሌምና በይሁዳ አገር ሁሉ ያሉትን እንዲሁም አረማውያንን ጭምር ንስሐ ገብተው ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ አስተማርሁአቸው ....." (የሐ.ሥ 26:19-20) ።

ሐዋርያ ጳውሎስ በተሰሎንቄ ከተማ ስለሚገኙት ክርስቲያኖች ሲናገር እንዲህ ይላል ፥ " ወደ እናንተ በመጣን ጊዜ እንዴት እንደተቀበላችሁን ፥ ሕያውና እውነተኛ የሆነውን አምላክ ለማምለክ ከጣዖቶች ወደ እግዚአብሔር እንዴት እንደተመለሳችሁ እነርሱ ራሳቸው ስለ እኛ ይመሰክራሉ " (1ተሰ 1:9) ።

## የማስታረቅ አገልግሎት

ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር የመመለስ አገልግሎት የማስታረቅ አገልግሎት ነው ። የማስታረቁን አገልግሎትና የእርቁን ጠባይ በበለጠ ለመረዳት አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ከዚህ በታች



እንመልከት ።

"ስለዚህ እናንተ ቀድሞ በትውልዳችሁ አረማውያን የነበራችሁ ፥ አይሁዳውያን በሰው እጅ በመገረዛቸው እየተመኩ እናንተን ያልተገረዙ እያሉ ይሰድቡአችሁ እንደነበር አስታውሱ ። የእስራኤልን ዜግነት አጥታችሁ ለተስፋው ቃል እንግዶች ሆናችሁ ፥ በዚህ ዓለምም ተስፋ አጥታችሁና ከእግዚአብሔር ተለይታችሁ ያለ ክርስቶስ ነበራችሁ ። አሁን ግን ፥ እናንተ ከዚህ በፊት ርቃችሁ የነበራችሁ ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ሆናችሁ በእርሱ ደም ቀርባችኋል ። ለያይቶን የነበረውን የጥል ግድግዳ ያፈረሰና አይሁዳውያንና አሕዛብን አንድ ያደረገ ሰላማችን ክርስቶስ ነው ። ሰላምንም በማድረግ ከሁለቱ ሕዝቦች ከእርሱ ጋር የሚተባበር አንድ አዲስ ሕዝብ ለመፍጠር የሕግን ትእዛዞችና ደንቦች በሥጋው ሻረ ። በመስቀል ላይ በመሞትም ጠላትነትን አስወገደ ፤ ሁለቱንም አንድ አካል አድርጎ ከእግዚአብሔር ጋር አስታረቃቸው ። መጥቶም ለእናንተ ርቃችሁ ለነበራችሁና ቀርበው ለነበሩት ለእነርሱም የሰላምን የምሥራች ቃል ሰበከ ። ምክንያቱም በእርሱ አማካይነት ሁላችንም በአንድ መንፈስ ተመርተን ወደ አብ እንቀርባለን" (ኤፌ 2:11-18) ።

ከዚህ በላይ የተመለከትነው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ብዙ ትምህርተ ሃሳቦችን የያዘ ነው ። ከነዚህ ሃሳቦች ጥቂቶቹን እንመልከት።

1ኛ/ በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል የጥል ግድግዳ ነበር ። ይህ አህዛብንም እሥራኤላውያንንም ያጠቃልላል ። የጥሉ ግድግዳ የኃጢአት ግድግዳ ነው ።

ስለዚህ ጉዳይ ኢሳያስ እንዲህ ሲል ተናገረ ፤ "ነገር ግን

በደላችሁ በእናንተና በአምላካችሁ መካከል ለይታለች ፤ እንዳይሰማ ኃጢአታችሁ ፊቱን ከእናንተ ሰውሮታል ” (ኢሳ 59:2) ።

2ኛ/ በእሥራኤልና በአሕዛብ ሕዝቦች መካከል የጥል ግድግዳ ነበር ። ይህ ግድግዳ በአንዱ ብሔረሰብና በሌላው ብሔረሰብ መካከል የነበረ መለያየት ነው ።

3ኛ/ እግዚአብሔርንና እነዚህን በኃጢአታቸው ምክንያት ከእግዚአብሔር ጋር የተለያዩትን የዓለም ሕዝቦች ለማስታረቅ ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጣ ። በመስቀል ላይ በመሞትና ከሞት በመነሳት ይህን እርቅ አከናወነ ።

4ኛ/ የሰው ልጆች ከአምላካቸው ጋር በመታረቃቸው እርስ በርስም ለመታረቅ ቻሉ ። በሕዝቦች መካከልና በብሔረሰቦች መካከል የነበረው የመለያየት ግድግዳ ተወገደ ።

5ኛ/ እነዚህ በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ ምክንያት ከእግዚአብሔርና እርስ በርስ የተራራቁት ነገዶችና ሕዝቦች “አንድ አዲስ ሕዝብ ” እና “አንድ አካል ” ሆኑ ።

ይህ “ አንድ አዲስ ሕዝብ ” ወይም “ አንድ አካል” ቤተ ክርስቲያን ነው ። ቤተ ክርስቲያን / ክርስቲያኖች ልዩ የሆነ ሰማያዊ ብሔረሰብ ነው ። ስለዚህ ሰማያዊ ብሔረሰብ ማንነትና ተልእኮ ጨምረን ብንመለከት የበለጠ ሰፋ ያለ ግንዛቤ ይሰጠናል።

“ ስለዚህ ማንም ከክርስቶስ ጋር ቢተባበር አዲስ ፍጥረት ነው ፤ አሮጌው ፍጥረት አልፎአል ። በእርሱ ስፍራ አዲስ ፍጥረት ተተክሎአል ። ይህም ሁሉ የሆነው እኛን ከራሱ ጋር በክርስቶስ



አማካይነት ባስታረቀንና የማስታረቅንም አገልግሎት በሰጠን በእግዚአብሔር ነው ። ይህም እግዚአብሔር በክርስቶስ አማካይነት ሰዎችን ሁሉ ከራሱ ጋር አስታረቀ ማለት ነው ። በደላቸውንም አልቆጠረባቸውም ፤ ለኛም የማስታረቅን ቃል ሰጠን ።

እግዚአብሔር ሰዎችን በእኛ አማካይነት ስለሚጠራ እኛ በክርስቶስ ስም አምባሳደሮች ነን ፤ ስለዚህ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን በክርስቶስ ስም እንለምናችኋለን (2ቆሮ 5:17-18)”።

ይህን ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ቀደም ብለን በኤፌ 2:11-18 ከተመለከትነው ትምህርት ጋር ስናስተያየው ስለ ቤተ ክርስቲያን ተልእኮ የበለጠ ጥርት አድርጎ ያሳየናል።

በዚህ በ2ቆሮ 5:17-20 የሰፈረው አሳብ አራት ፍሬ ነገሮችን ያስተምረናል ።

1ኛ/ እግዚአብሔር ሰዎችን ከነገድና ከቋንቋ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ከራሱ ጋር እያስታረቀ ነው ።

2ኛ/ እግዚአብሔር ለእነዚህ ከእርሱ ጋር ለታረቁት ሰዎች ወይም “አንድ አዲስ ሕዝብ ” ወይም “አዲስ አካል ”(ቤተ ክርስቲያን ) “የማስታረቅን አገልግሎት ” ሰጠ ። ይህ የማስታረቅ አገልግሎት የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ ነው ።

3ኛ/ እነዚህ መልእክተኞች /ቤተ ክርስቲያን “ ከማስታረቅ አገልግሎት ” ጋር “የማስታረቂያም ቃል ” ተቀበሉ ። ይህ “የማስታረቂያ ቃል ” የወንጌል ቃል ነው ።

4ኛ/ እነዚህ "የማስታረቅን አገልግሎት " እና "የማስታረቂያን ቃል " የተቀበሉት "አዲስ ሕዝብ " ወይም ቤተ ክርስቲያን "የክርስቶስ አምባሳደሮች " ናቸው ። ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስን በመወከል " ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ " እያለች ወንጌልን ታውጃለች ማለት ነው ።

ቤተ ክርስቲያን ለአገር እድገትና ሰላም ትጸልያለች ። ነገር ግን አገርን አትወክልም ። ቤተ ክርስቲያን የምትወክለው የቤተ ክርስቲያን እራስ የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን ነው ።

ቤተ ክርስቲያን ብሔረሰብን ሁሉ በእግዚአብሔር ዓይን እያየች ፥ በእግዚአብሔር ፍቅር እየወደደችና እያከበረች ሁሉንም በእኩልነት ማገልገል አለባት ። ይሁን እንጂ ቤተ ክርስቲያን ማንኛውንም ብሔረሰብ አትወክልም ።

ኢየሱስ ክርስቶስን በመወከል ሁሉንም ብሔረሰብ በወንጌል አገልግሎት ታገለግላለች ። ስለሆነም ቤተ ክርስቲያን አገርን ፥ ብሔረሰብን ፥ ቋንቋን አትወክልም ። ሕዝቡ ሰምቶ በሚረዳው ቋንቋ የወንጌልን አዋጅ ታስተላልፋለች ።

ቤተ ክርስቲያን በአገር ፍትህ የፖለቲካ አቋም ፥ መልካም የኢኮኖሚ እድገትና የህብረተሰብ አንድነት እንዲኖሩ መጸለይ ይኖርባታል ። ነገር ግን ራሷ የአንድ የፖለቲካ ቡድን ወይም ፓርቲ ወኪል መሆን ተልእኮዋ አይደለም ። ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር መንግሥት ወኪል በመሆን የዚህን መንግሥት አዋጅ ማወጅ አለባት ።



ሰዎች በግለሰብም ደረጃ ሆነ በብሔረሰብ ደርጃ ከእግዚአብሔር ጋር ፥ ሲታረቁ ግለሰብም ከግለሰብ ጋር ብሔረሰብም ከበሔረሰብ ጋር ይታረቃሉ ።

በዚህ እጅግ በከፋው ዘመናችን በግለሰቦች መካከልና በብሔረሰቦች መካከል ያለውን መለያየት ፥ ጥላቻ ፥ መናናቅ ፥ መዋጋትና መደማሰስ ለማስወገድ የሚቻለው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ብቻ ነው ።

ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን እንደ " አንድ አዲስ ሕዝብ " ወይም እንደ ክርስቶስ " አምባሳደር " ይሆን " የማስታረቂያ " ቃል ወይም የክርስቶስ ወንጌል በታማኝነት ለነገድና ለቋንቋ ሁሉ ማወጅ አለባት ። ይህ ሰማያዊ አዋጅ ነው የሰዎችን ልብ ወደ እግዚአብሔር የሚመልሰው ።

ሰዎች አንድ ዓይነት ቋንቋ ስለሚናገሩ ብቻ አንድነትና ሕብረት ሊኖራቸው አይችልም ። ከአንድ ብሔረሰብ ስለሆኑ ብቻ ፥ በአንድ አካባቢ ስለተወለዱ ብቻ አድነትና ሕብረት ሊኖራቸው አይችልም ።

ለሰዎች አንድነትንና ሕብረትን ሊያስገኝ የሚችለው የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ብቻ ነው ። የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ለሰዎች አንድነትንና ሕብረትን ከማስገኘትም አልፎ አንድ ቤተሰብ ያደርጋል።

የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል የብሔረሰብነትን ግድግዳ አፈራርሶና የቋንቋን አጥር ደምስሶ ነገድንና ቋንቋን አንድ ቤተሰብ ፥ ያውም የሕያው እግዚአብሔር ቤተሰብ ያደርጋል ።

ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር መመለስ የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ መሠረታዊ ነገሮች ከሆኑት አንዱ ክፍል ነው ። ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር መመለስ ስንል ምን ማለታችን ነው ?

በኢሳይያስ 53:6 " እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን ከኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ ....." ሲል ሰዎች በኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር መለየታችንን ያሳየናል ። ሐዋርያ ጴጥሮስ በአንደኛ መልእክቱ 2:25 ይህን አሳብ እያይዞ ሲጽፍ እንዲህ ይላል ፤ " ....እናንተ እንደ ጠፉ በጎች ትቅበዘበዙ ነበር ፤ አሁን ግን ወደ ነፍሳችሁ እረኛና ጠባቂ ተመልሳችኋል ። "

እረኛ እንደሌላቸው በጎች ፣ እውነተኛ መንገድ እንደ ጠፋቸው መንገዶች የተቅበዘበዙት ሰዎች ወደ እውነተኛው አምላክ ሲመለሱ ፣ ስለ ኃጢአታችን በመስቀል ላይ የሞተልንን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ይተዋወቃሉ ።

በመገረፉ ቁስል የፈወሰንን (1ኛ ጴጥ 2:24)፣ ሕይወቱን ስለ በጎቹ አሳልፎ የሰጠውን መልካሙን እረኛ (ዮሐ 10:11) ፣ የነፍሳችን እረኛና ጠባቂ የሆነውን (1ጴጥ 2:25)ውዱን ኢየሱስ ክርስቶስን ያገኛሉ ።

ላለፈው ኃጢአታቸው ይቅርታን ተቀብለው የዘላለም ሕይወት የሆነውን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ይቀበላሉ ። " ወደ እግዚአብሔር መመለስ " የሚለው አሳብ ሶስት ቁምነገሮችን ያጠቃልላል ።

1ኛ/ ሰው ኃጢአተኛ መሆኑን በማመን ፣ ስለ ኃጢአቱ በመስቀል ላይ የሞተለትን የእግዚአብሔርን ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስን



እንደግል አዳኙ መቀበል ይኖርበታል ።

2ኛ/ በማቴዎስ 28:19 እንደተጻፈው ፣ በአብ ፣ በወልድ ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም በውሃ መጠመቅ አለበት ።

3ኛ/ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው ተቀብለው ፣ በእውነትና በመንፈስ እግዚአብሔርን ከሚያመልኩት የክርስቲያን ጉባኤ የአካል ክፍል በመሆን እግዚአብሔርን ማምለክና ማገልገል ይኖርበታል ።

አንዳንድ ሰዎች ስለ ቤተ ክርስቲያን ተልእኮ ወይም ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር ስለ መመለስ ሲናገሩ ፣ ቤተ ክርስቲያን ቃሉን በታማኝነት ካወጀች ተልእኮዋን ፈጸመች በማለት የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ እዚሁ ላይ የሚያበቃ አስመስለው ይናገራሉ ። ይህም ማለት ፣ ሰዎች የቃሉን መልእክት ሰምተውና አምነው ወደ እግዚአብሔር ቢመለሱም ባይመለሱም ቤተ ክርስቲያን የሚገባትን ተልእኮ ፈጽማለች ማለታቸው ነው ።

እውነት ነው ቤተ ክርስቲያን የጌታን ቃል በታማኝነትና በእውነት ማወጅ አለባት ። ቤተ ክርስቲያን ሰዎችን በግድ ማሳመን አትችልም ። ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር እቅድ ቤተ ክርስቲያንን ሊሠራ እንደ ሆነ ቃሉ ይመሰክራል (ማቴ 16:18) ።

ጌታ ኢየሱስ " ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ " ሲል " ሕንፃ " እሰራለሁ ማለቱ አይደለም ። ቤተ ክርስቲያን ማለት የክርስቲያኖች ክምችት ወይም ጉባኤ ማለት ነው ። ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው የተቀበሉና በቅዱስ ደሙ የነጹ የክርስቲያኖች ጉባኤ ወይም ክምችት " ቤተ ክርስቲያን "ይባላል።

ስለ ሆነም ቤተ ክርስቲያን ቃሉን ማወጅ ብቻ ሳይሆን ሰዎችን በቃሉ ማሳመን ፥ በአብ ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ማጥመቅ ፥ እነዚህን ሰዎች ወደ ክርስቲያኖች ጉባኤ እንዲደባለቁና አንድ አካል እንዲሆኑ ማድረግ አለባት ።



# ምዕራፍ 4

## ቤተ ክርስቲያን በቁጥር የምታድግበት ዘዴ

ቤተ ክርስቲያን በቁጥር የምታድግበትን ዘዴ ከመዘርዘሬ በፊት ለሁላችንም ግልጽ የሆኑትን አንዳንድ ነጥቦች ልጥቀስ ።

1ኛ /ጸሎት :-

የወንጌል አገልግሎት በጸሎት ካልተጀመረና ሳይሰለች ሁል ጊዜ በጸሎት ካልታጀበ አጥጋቢ ፍሬ ሊያስገኝ አይችልም ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእለቱን የወንጌል አገልግሎት ከመጀመሩ በፊት ጊዜ ወስዶ ይጸልይ ነበር ። “ ሊነጋጋ ሲል ኢየሱስ በማለዳ ተነስቶ ወጣና ለመጸለይ ወደ አንድ ገለልተኛ ቦታ ሄደ ” ( ማር 1:35 ) ።

እንዲሁም የእለቱን የወንጌል አገልግሎት ከጨረሰ በኋላ ያንን አገልግሎት በጸሎት ያጅበው ነበር ። " ሕዝቡንም ካሰናበተ በኋላ ለመጸለይ ብቻውን ወደ አንድ ተራራ ላይ ወጣ ፤ በመሸም ጊዜ ኢየሱስ እዚያ ብቻውን ነበር " ( ማቴ 14 : 23 ) ።

የሐዋርያት የወንጌል አገልግሎት በጸሎት የተቀደመና በጸሎት የታጀበ ነበር ። " ከጸለዩ በኋላ የነበሩበት ስፍራ ተናወጠ ፤ ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ ፤ የእግዚአብሔርንም ቃል ያለ ፍርሃት በድፍረት ተናገሩ " ( የሐ ሥ 4:31 ) ።

በወንጌል አገልግሎት ውስጥ የጸሎትን አስፈላጊነት የተረዳ ሐዋርያ ጳውሎስ የምእመናንን የጸሎት እርዳታ እንዲህ ሲል ይጠይቃል ፤ " የወንጌልን ምስጢር ያለ ፍርሃት እንድገልጽ ፥ በምናገርበት ጊዜ አስፈላጊዉን ቃል እንዲሰጠኝ ለእኔም ጸልዩልኝ ። አሁን እንኳ ታስሬ ሳለሁ የዚህ ወንጌል አምባሳደር ነኝ ፤ ስለዚህ እንደሚገባኝ ያለ ፍርሃት እንድናገር ጸልዩልኝ " ( ኤፌ 6:19-20 ) ።

ጳውሎስ ለቃሉ መገለጥና ለድፍረት የምእመናንን የጸሎት እርዳታ እንደጠየቀ ሁሉ እግዚአብሔር የአገልግሎትም በር እንዲከፍትለት በጸሎት ሲጠይቅ ይታያል ። " እግዚአብሔር ለምሥራቹ ቃል በር እንዲከፍትልኝና በእርሱ ምክንያት እኔ ታስሬ የምገኝበትን የክርስቶስን ምስጢር ማብሠር እንድችል ለእኛም ጸልዩ " ( ቆላ 4 : 3 ) ።

ቤተ ክርስቲያን የወንጌሉን የምስራች ቃል ስታውጅ ፥ የቃሉን ዘር ስትዘራ መዘንጋት የሌለባት ነገሮች



አሉ ።

1ኛ/ የወንጌሉ ብርሃን እንዳያበራላቸው ሰይጣን የኃጢአተኞችን ልቦና እንደሚያሳውር ፥ እንደሚያጨልም ማሰብ ያስፈልጋል ። "ያበሰርነው የምሥራች ቃል ምናልባት የተሰወረ ቢሆንም ፥ የተሰወረው ለሚጠፉት ነው ። እነርሱ የማያምኑበት ምክንያት የዚህ ዓለም አምላክ የሆነው ሰይጣን ልቦናቸውን ስላሳወረው ነው ፤ በእግዚአብሔር መልክ ስለተገለጠው ስለ ክርስቶስ ክብር ከተነገረው መልካም ዜና የሚመጣላቸውን ብርሃን እንዳያዩ ያደረጋቸው እርሱ ነው " ( 2ቆሮ 4 : 3-4 ) ።

2ኛ/ ሰይጣን የተዘራው የወንጌል ቃል ፤ የታወጀው የምሥራች መልእክት በሰሚዎች ልብ ቦታ እንዳያገኝና በቅሎ ፍሬ እንዳያገኝ በተቻለ መጠን ዘሩን ከልባቸው እየለቀመ እንደሚወስድ መረዳት ያስፈልጋል ።

ጌታችን ኢየሱስ ይህን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ይላል ፥ " ዘሩ የእግዚአብሔር ቃል ነው ፤ በመንገድ ዳር የወደቀው ዘር የሚያመለክተው ቃሉን ለጊዜው የሚሰሙትን ሰዎች ነው ፤ ነገር ግን እነርሱ አምነው እንዳይድኑ ዲያብሎስ መጥቶ ቃሉን ከልባቸው ይወስዳል " ( ሉቃ 8:11-12 ) ።

ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን በጸሎት ኃይል ሶስት ነገሮችን ታደርጋለች ። አንደኛ :- የጠላትን ፥ የሰይጣንን ምሽግ ማፈራረስ ነው ።

ሁለተኛ :- ጠላትን / ሰይጣንን ማሰር ነው ። " ደግሞስ አንድ ሰው አስቀድሞ ኃይለኛዉን ሳያስር ወደ ኃይለኛው

ቤት ገብቶ ንብረቱን መዝረፍ እንዴት ይችላል ? ኃይለኛዉን ካሰረው በኋላ ግን ንብረቱን ሊዘርፍ ይችላል " ( ማቴ 12:29 ) ።

ሶስተኛ :- ጠላት / ሰይጣን በኃጢአት እስራት ተብትቦ የያዛቸውን ነፍሳት በማስለቀቅ ለክርስቶስ ምርኮን መማረክ ነው ። " ኃይለኛውን ካሰረው በኋላ ግን ንብረቱን ሊዘርፍ ይችላል " ( ማቴ 12:29 ) ።

2ኛ/ መንፈስ ቅዱስ :-

ሐዋርያት የወንጌልን አዋጅ ያወጁት በመንፈስ ቅዱስ ጥበብና ኃይል ነበር ።ያለ መንፈስ ቅዱስ ኃይል የጌታን ወንጌል ለማብሰር አይቻልም ። ያለ መንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚታወጅ ወንጌል ፍሬ አያፈራም ። ለዚህ ነው የወንጌሉ ባለቤት የወንጌሉን መልእክተኞች እንዲህ ሲል ያሳሰባቸው ፥ " ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእነንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ ፤ በዚያን ጊዜ በኢየሩሳሌም ፥ በይሁዳ አገር ሁሉ ፥ በሰማርያ ፥ እስከምድር ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ "( የሐ ሥ 1:8) ። በጴንጤቆስጤ በዓል ቀን በመንፈስ ቅዱስ የታወጀው የምሥራች ቃል የጠላትን ይዞታ ደምስሶ ሶስት ሺህ የሚያህሉትን ነፍሳት ለክርስቶስ አስማረከ ( የሐ ሥ 2 ) ።

መኪና በመሬት ለመሽከርከር ፥ አውሮፕላን በሰማይ ለምብረርና መርከብ በውቅያኖስ ላይ ለመንሳፈፍ ሁል ጊዜ በቤንዚን መሞላት አለባቸው ። ቤተ ክርስቲያንም የክርስቶስን ወንጌል በኃይልና በጥበብ ለማወጅ የምትችለው ዘወትር በመንፈስ ቅዱስ



ስትሞላ ነው ። የመንፈስ ቅዱስ ሙላት የአንድ ጊዜ ልምምድ አይደለም ።

በጴንጠቆስጤ ቀን በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ሶስት ሺህ የሚያህሉትን ነፍሳት ለጌታ የማረከው ጴጥሮስ እንደገና በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ወንጌሉን ማወጅ እንዳስፈለገው ተጽፎ እናገኛለን።

" በዚህ ጊዜ ጴጥሮስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ እንዲህ ሲል መለሰላቸው ፥ እናንተ የሕዝብ አለቆችና ሽማግሌዎች ሆይ ! እኛ ዛሬ የምንጠየቀው ለአንድ ሽባ ሰው ስለተደረገለት መልካም ሥራና በምን ዓይነት ሁኔታ እንደዳነ ነው ። ይህ ሰው ድኖ በፊታችሁ የቆመው ፥ እናንተ በሰቀላችሁትና እግዚአብሔርም ከሞት ባስነሳው በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንደሆነ ለእናንተ ለሁላችሁም ለእስራኤል ሕዝብ ሁሉ የታወቀ ይሁን " ( የሐ ሥ 4:8-10 ) ።

የሐዋርያትን ሥራ ስንመለከት የወንጌል አወጃ እንደቀጠለ ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ መሞላትም እንደቀጠለ እንገነዘባለን ። በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ የማገልገሉ ወይም ወንጌልን የማወጁ ነገር የጥቂት ሐዋርያት ድርሻ ወይም እድል ፈንታ አልነበረም ። የአገልጋዮች ሁሉ ልምምድና እድል ፈንታ ነበር ። " ከጸለዩ በኋላ የነበሩበት ስፍራ ተናወጠ ፤ ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ ፤ የእግዚአብሔርንም ቃል ያለ ፍርሃት በድፍረት ተናገሩ " (የሐ ሥ 4:31 )። በእነዚህ እንደገና በመንፈስ ቅዱስ ከተሞሉት አገልጋዮች መካከል ጴጥሮስና ዮሐንስ ይገኙባቸዋል ። ዛሬ እኛ የምናውጀው ወንጌል ያው እነ ጴጥሮስ ያወጁት ወንጌል ከሆነ ፥ እኛም እነርሱ ባወጁበት የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተሞልተን ማወጅ ግዴታችንም እድል ፈንታችንም ነው ።

3ኛ/ፍቅር:-

ፍቅር በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ለእግዚአብሔርም ሆነ ለሰዎች ለምናደርጋቸው ነገሮች ሁሉ ወሳኝ ነው ። የክርስቶስ ወንጌል መሰረት ፍቅር ነው ። ከሙሴ ሕግ መምህራን መካከል አንዱ ወደ ኢየሱስ መጥቶ ከትእዛዛት ሁሉ የሚበልጥ የትኛው ትእዛዝ እንደሆነ በጠየቀው ጊዜ ኢየሱስ ከዚህ የሚከተለውን መልስ ሰጠው ፤ " እግዚአብሔር አምላክህን በፍጹም ልብህ ፥ በፍጹም ነፍስህ ፥ በፍጹም አሳብህ ውደድ ፤ ከሁሉም የሚበልጠው የመጀመሪያው ትእዛዝ ይህ ነው ። ይህንንም የሚመስለው ሁለተኛው ትእዛዝ ሰውን ሁሉ እንደ ራስህ አድርገህ ውደድ የሚለው ነው " ( ማቴ 22:37-38 ) ።

እግዚአብሔር ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን የመስዋእት በግ አድርጎ የሰጠን ስለ ወደደን ነው ። " እግዚአብሔር ዓለምን እጅግ ስለ ወደደ አንድ ልጁን ሰጠ ፤ ስለዚህ በልጁ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት ይኖረዋል እንጂ አይጠፋም " ( ዮሐ 3:16 ) ።

ይህ አስገራሚ ፍቅር በጎልጎታ ተራራ ላይ በተግባር ከተገለጠ በኋላ የዚህ ፍቅር ሥራ ተጠቃሚ የሆነው ጳውሎስ ስለዚህ ታላቅ ፍቅር ሲገልጥ እንዲህ አለ ፤ " ነገር ግን እኛ ኃጢአተኞች ሆነን ሳለ ክርስቶስ ስለእኛ ሞተ ይህም እግዚአብሔር ስለእኛያለው ፍቅር ምን ያህል ታላቅ መሆኑን ያስረዳል " ( ሮሜ 5:8 ) ።



እንግዲህ ነፍሳትን በክርስቶስ ወንጌል ለመድረስ የምንችለው ለእግዚአብሔርና ለነፍሳት ፍቅር ሲኖረን ብቻ ነው ። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ ጴጥሮስን ሶስት ጊዜ ደጋግሞ ጥያቄ ጠየቀው ። የጠየቀው ጥያቄ ፥ " የዮና ልጅ ስምኦን ሆይ ! ትወደኛለህን ? " ( ዮሐ 21:15-17 ) የሚል ነበር ። ኢየሱስ ከጴጥሮስ የአዎታ መልስ ካገኘ በኋላ " ግልገሎቼን መግብ " ፥ " ጠቦቶቼን ጠብቅ " ፥ " በጎቼን አሠማራ " ( ዮሐ 21:15-17 ) ሲል የአገልግሎትን መመሪያ ሰጠው ።

ሐዋርያ ጳውሎስ ስለዚህ ፍቅር ሲናገር እንዲህ ይላል ፥ " አንድ ጊዜ ክርስቶስ ለሁሉም መሞቱንና ሁሉም የእርሱ ሞት ተከታዮች መሆናቸውን ስለ ተረዳን የክርስቶስ ፍቅር ለሥራ ይገፋፋናል " ( 2ቆሮ 5:14 ) ። በወንጌል አገልግሎት ምክንያት ሮም በነበርሁ ጊዜ ፥ ጴጥሮስ የታሠረበትንና ቁልቁል ተሰቅሎ የሞተበትን ቦታ አየሁ ። እንዲሁም ጳውሎስ የታሠረበትንና ጭንቅላቱን በመደሻ ሶስት ቦታ በመተርተር የተገደለበትን ቦታ አየሁ ። ቆም ብዬ በተመስጦ አሰብሁ ። በርግጥ ፥ ያ ፍቅር ፥ ያ ለእግዚአብሔርና ለነፍሳት የነበራቸው ፍቅር እስከ ምን ድረስ " ግድ " እንዳላቸው በጥልቀት አስተዋልሁ ።

እዚህ ላይ አንድ ነገር እንዳይዘነጋ ላሳስብ እወዳለሁ ። ለእግዚአብሔርም ለነፍሳትም ፍቅር ሳይኖረን የምስራቹን ቃል ለማወጅ ይቻላል ። ነቢዩ ዮናስ ለንስሐ የሚያበቃን የእግዚአብሔርን መልእክት ለነነዌ ሕዝብ አስተላልፎ ነበር ። ነገር ግን ተጽፎ እንደምናገኘው ፥ ነቢዩ ዮናስ ለእግዚአብሔርም ሆነ ለነነዌ ሕዝብ ፍቅር አልነበረዉም ። ሰዎቹ ንስሐ መግባታቸውና እግዚአብሔር ሕዝቡን በይቅርታ መቀበሉ ዮናስን አላስደሰትዉም ። እንዲያውም አበሳጨው ።

የእግዚአብሔር እሳት ከሰማይ ወርዶ የነነዌን ሕዝብና ከተማ አመድ ቢያደርገው ቅር አይለውም ነበር ። ዮናስ ዘረኛም እንደነበር ግልጽ ነው ። ዛሬም ቤተ ክርስቲያን ልቧንና አገልግሎትዋን መመርመር አለባት ። የዘረኝነት መንፈስ ሁሉንም በአምሳሉ ከፈጠረው ከእግዚአብሔር አይደለም ። የዘረኝነት መንፈስ የእግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ጠላት ከሆነው ከዲያቢሎስ ነው ። የዘረኝነት መንፈስ የተረገመ ይሁን !

ቤተ ክርስቲያን ያለ ማቋረጥ በጸሎት ስትጋደል ፣ ሁልጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ስትሞላ ፣ ለእግዚአብሔርና ለነፍሳት እውነተኛ ፍቅር ሲኖራት ብቻ ነው የቋንቋን ፣ የብሔረሰብን ፣ የጂኦግራፊን ፣ የሐብትንና የድህነትን ክልል ሁሉ አልፋ የምሥራቹን ቃል ለማወጅ የምትችለው ።

ተልእኮዋችን ሰማያዊ ነው ! አዋጃችን ፣ ወንጌላችን የማይሻር ነው ! መስካችን ድንበር የለዉም ! ሥራችን ገና አላለቀም!

## የእድገት ዘዴ

ቤተ ክርስቲያን በመንፈሳዊ ሕይወትም በቁጥርም እንድታድግ የእግዚአብሔር ፍላጎት እንደሆነ ቀደም ብለን ተመልክተናል ። ይህ ምን ጊዜም የማይለወጥ የእግዚአብሔር እቅድ ነው ። ስለሆነም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ይህን የእግዚአብሔር እቅድ በአእምሮዋ ይዛ አገልግሎትዋን ማካሄድ አለባት ።



ይህ ዘላለማዊ የእግዚአብሔር እቅድ እየተፈጸመ ይሄድ እንደሆነ ወይም አይሄድ እንደሆነ ለመረዳት ቤተ ክርስቲያን ዘወትር አገልግሎትዋን መመዘን አለባት ። አገልግሎትዋን ስትመዝን ራስዋን መጠየቅ ካሉባት ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች መካከል ከዚህ የሚከተሉት ነጥቦች መገኘት አለባቸው ።

1ኛ/ የሚድኑት ነፍሳት እየተጨመሩ ይሄዳሉ ?

2ኛ/ ምእመናኗ በመንፈሳዊ ሕይወት እየታነጹና እያደጉ ይሄዳሉ ?

3ኛ/ በልዩ ልዩ የአገልግሎት ዘርፎች ተሰልፈው ጌታቸውን የሚያገለግሉ አገልጋዮች እያፈራች ትሄዳለች ?

4ኛ/ ለምእመናኗ አጥጋቢ የሆነ አገልግሎት ትሰጣለች?

በጠቅላላው እግዚአብሔር ለዚያች አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ያለው እቅድ እየተከናወነ ነው የሚሄደው ?

ቤተ ክርስቲያን እነዚህን ጥያቄዎች ስትጠይቅ በእውነተኛ መንፈስ መጠየቅ አለባት ። ራሷን ማታለል የለባትም ። ድካሟን ለማየትና ስህተቷን ለመቀበል ፈቃደኛ መሆን አለበት ። አገልግሎትዋን በየጊዜው ካልመዘነችና እነዚህን ጥያቄዎች ራሷን ካልጠየቀች ደካማ ጎንዋን ለማየትና ስህተቷን ለመረዳት አትችልም ።

ደካማ ጎንዋን ካላወቀችና ስህተቷን ካልተገነዘበች ፣ ለመሻሻል ለመታረም ፣ ለማደግና የእግዚአብሔር እቅድ በአገልግሎትዋ

እንዲፈጸም ለማድረግ አትችልም ።

በየጊዜው አገልግሎትዋን በእውነተኛ መንፈስ በመመዘን ፣ መታረም ያለባቸውን ነገሮች እያረመችና መስተካከል ያለባቸውን ነገሮች እያስተካከለች ከተጓዘች ማደጓ የማያጠራጥር ነው ። እግዚአብሔርም የሚድኑትን ነፍሳት በየጊዜው ወደ ጉባኤው ይጨምራል ። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ፈቃድ ቤተ ክርስቲያኑ " በሁሉ " ነገር እንድታድግ ነው ( ኤፌ 4:15 ) ።

ቤተ ክርስቲያን በአምስት መንገዶች በቁጥር ልታድግ ትችላለች ። እነዚህን የእድገት መንገዶች ወይም ዘዴዎች ከዚህ ቀጥዬ እዘረዝራለሁ ።

## የሚድኑትን ሰዎች ወደ ጉባኤ በመጨመር

የቁጥር እድገት ማለትም የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ቁጥር ማደግ የማይለወጥ ፍጹም የሆነ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ። በልዩ ልዩ የምዕራብ አገሮች (በተለይ በአዉሮፓ አገሮች ለወንጌል አገልግሎት ስዘዋወር የተመለከትሁት አሳዛኝ ነገር አለ ። በእነዚህ አገሮች ከብዙ ዓመታት በፊት የክርስቶስ ወንጌል በታላቅ ኃይል ይሰበክ ነበር ። ከዚህ የተነሳ በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠሩ ነፍሳት ወደ እግዚአብሔር ተመለሱ ። ለእነዚህ ምእመናን ማምለኪያ ቦታዎች የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ህንጻዎች በየቦታው ተሠሩ ። በእነዚህ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር በመንፈስና በእውነት ይመለክ ነበር ።

ህንጻዎች በየቦታው ተሠሩ ። የክርስቶስ ወንጌል ሳልዳኑት



ይሰበክ ነበር ። ዛሬ ግን ከእነዚህ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሕንፃዎች መካከል ግማሾቹ ባዶአቸውን ቀርተዋል ። አንዳንዶቹም ለዓለማውያን ተሸጠው ለልይ ልዩ ጥቅም እየዋሉ ናቸው ።

ይህ ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም ። እነዚህን ሕንጻዎች በማየትና የእነዚህን አገሮች ሁኔታ በማሰብ ብዙ ጊዜ እንባዬን አፍስሼ አልቅሻለሁ ። በአሁኑ ጊዜ ለእነዚህ አገሮች ያለ ማቋረጥ በምልጃ ጸሎት በዙፋኑ ፊት እንድቃትት እግዚአብሔር ትልቅ ሸክም አሸክሞኛል ።

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እድገት የእግዚአብሔር ፍጹም ፈቃዱ መሆኑንን ለመገንዘብ የሐዋርያት ሥራን መመልከት ብቻ ይበቃል ።

የመጀመሪያዎቹ አማኞች ቁጥር :-" በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ መቶ ሃያ በሚያህሉ አማኞች መካከል ቆመና እንዲህ አለ " ( የሐ ሥ 1:15 ) ።

በጰንጠቆስጤ በዓል ቀን ወደዚህ ጉባኤ የተጨመሩ አማኞች ቁጥር :-" ከእነርሱ ብዙዎቹ ቃሉን ተቀብለው ተጠመቁ ፤ በዚያን ቀን ሶስት ሺህ የሚያህሉ አማኞች ተጨመሩ " ( የሐ ሥ 2:41 ) ።

በጰንጠቆስጤ በዓል ቀን ሶስት ሺህ የሚያህሉ ነፍሳት ከተጨመሩ በኋላ :-" እግዚአብሔርንም ያመሰግኑ ነበር ፤ ሰዉም ሁሉ ያከብራቸው ነበር ፤ እግዚአብሔርም የሚድኑትን ሰዎች በየቀኑ ወደ ማህበራቸው ይጨምር ነበር " ( የሐ ሥ 2:47 ) ።

ከሸባው ሰው መፈወስና ከጴጥሮስና ከዮሐንስ ስብከት በኋላ እንደገና ወደ ጉባኤ የተጨመሩ ነፍሳት ቁጥር :- “ ነገር ግን ቃላቸዉን ከሰሙት ሰዎች መካከል ብዙዎች አመኑ ፤ የአመኑትም ሰዎች ቁጥር ወደ አምስት ሺህ ከፍ አለ ” ( የሐ ሥ 4:4 ) ።

ከሐናንያና ሰጲራ ሞት በኋላ የጨመረው የነፍሳት ቁጥር :- “ በጌታ የሚያምኑ ወንዶችና ሴቶች ቁጥራቸዉ በጣም እየበዛ ይሄድ ነበር ” ( የሐዋ ሥ 5:14 ) ። ሰባቱ የማእድ አገልጋዮች ከመመደባቸው ቀደም ብሎ የነበርው የምእመናን ቁጥር :- “ ከጥቂት ጊዜ በኋላ የአማኞች ቁጥር እየበዛ ሲሄድ ........ ” ( ዮሐ ሥ 6:1 ) ።

ሰባቱ የማእድ አገልጋዮች ከተመደቡ በኋላ የነበረው የምእመናን ቁጥር :-“ በዚህ ሁኔታ የእግዚአብሔር ቃል እየትስፋፋ ስለሄደ በኢየሩሳሌም የአማኞች ቁጥር በጣም እየበዛ ሄደ ፤ ከካህናትም ብዙዎች አመኑ ” ( የሐ ሥ 6:7 ) ።

አሳዳጁ ጳውሎስ ከጥፋት መንገዱ ተመልሶ እጁን ለጌታችን ከሰጠ በኋላ የነበረው የምእመናን ቁጥር እድገት :-“ በይሁዳ አገር ፥በገሊላና በሰማርያ አገር ሁሉ ያለችው ቤተክርስቲያን ሰላም አገኘች ፤ በረታችም ፤ ጌታን እያከበረችና በመንፈስ እየተጽናናች በቁጥር አደገች ” ( የሐ ሥ 9:31 ) ።

የሐሰት ትምህርት በሕብረት ከታረመ በኋላ የተገኘው የምእመናን የቁጥር እድገት :- “ ስለዚህ አብያተ ክርስቲያኖች በእምነት ጠነከሩ ፤ ቁጥራቸውም በየቀኑ እየጨመረ ይሄድ ነበር ” ( የሐ ሥ 16:5 ) ።



እንግዲህ ስለ ምእመናን የቁጥር እድገት ፕሪንሲፕል እነሆ “እንደ ደመና በዙሪያችን የከበቡን እነዚህ ሁሉ ምስክሮች አሉልን ” ( ዕብ 12:1 ) ። ስለዚህ ለምእመናን ቁጥር እድገት መጸለይ ፥ ለእድገት መስበክና የሚድኑት ነፍሳት በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ተተክለው እንዲቀሩ አስፈላጊውን እንክብካቤ ማድረግ ግዴታችን ነው ።

## በቁጥር በጣም ያደገውን ጉባኤ በመክፈል

በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረተና ጤነኛ አገልግሎት ያለው የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አብዛኛዉን ጊዜ እንደሚያድግ የተወቀ ነው ። እድገቱ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ፤ የሚያስደስትም ነው ፤ መሆንም አለበት ።

ነገር ግን ከመጠን በላይ ካደገ ቶሎ ዘዴ ካልተፈጠረለት ችግር ሊያስከትል ይችላል ። በማስተዋል ዘዴ ከተፈጠረለት ግን የበለጠ ሊያድግና እድገቱም ጤነኛ እድገት ሊሆን ይችላል ። ይህ ዘዴ ይህን በቁጥር በጣም ያደገዉን የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በማስተዋል መክፈል ነው ። ይህ አደራረግ ሌላ ጤነኛ የሆነ እድገትን ያስገኛል ።

ይህን አስብ ከዚህ ቀጥዬ በዝርዝር ለማሳየት እሞክራለሁ ። “ ከመጠን በላይ ካደገ “ማለት ምን ማለት ነው ? መጠኑን በምን ሚዛን ነው የምንመዝነው ?

መጠኑ ወይም የምእመናኑ የቁጥር ብዛት የሚመዘነው

ETHIOPI... ...CAL CHURC
... RD.
DALLAS, TX 75218

እንደ አካባቢው ሁኔታዎች መታየት ያለበት ጉዳይ ነው ። ከእነዚህ መካከል ሰባት ዋና ዋና ነገሮችን እጠቅሳለሁ ።

1ኛ/ የመሰብሰቢያ ሕንፃ / አዳራሽ :-

የአጥቢያ የምእመናን የቁጥር እድገት ከሚያስከትለው ችግሮች መካከል አንዱ የቦታ ጥበት ነው ። አዳራሹ ወይም ሕንፃው ጠባብ ከመሆኑ የተነሣ ቃሉ በሚሰበክበትና የአምልኮት አገልግሎት በሚካሄድበት ጊዜ ምእመናን ሁሉ ቦታ ማግኘት አይችሉም ። ስለሆነም ግማሹ ወይም የሚበዙት ምእመናን በክረምት ዝናብ ውስጥ በመቆም ፥ በበጋ ደግሞ ጠራራ ጸሐይ ላይ በመቆም ቃሉን መስማትና እግዚአብሔርን ማምለክ ግድ ይሆንበቸዋል።

በተጨማሪም ፥ ( ከተማ ውስጥ ከሆነ ) የመኪናው ድምጽ ፥ የመንገደኞች ጫጫታና የነፋሱ ድምጽ ጆሮአቸውን ያውካል ። ይህን በመሰለ አካባቢና ሁኔታ ውስጥ ሆነው የእግዚአብሔርን ቃል እንደሚፈለግባቸው ለመስማትና በእውነትና በመንፈስ ጌታን ለማምለክ አስቸጋሪ ይሆንባቸዋል ።

በእነዚህ ሰዎች መካከል በእድሜ በጣም የገፉ አዛውንት ፥ የጤና ችግር ያለባቸው ሴቶችና ወንዶች ፥ ህፃናትን ያዘሉ እናቶችና ነፍሰ ጡር የሆኑ ሴቶች እንደሚኖሩ የታወቀ ነው።

እነዚህ ምእመናን ከዚህ በላይ በተጠቀሱት አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ሆነው ሁልጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል መስማትና ጌታን ማምለክ ስለሚከብዳቸው ተሰፋ ቆርጠው ከነጭራሹ ከቤተ ክርስቲያን ሊቀሩ ይችላሉ ። ይህ ደግሞ ማንንም አይጠቅምም ። ለእግዚአብሔርም ፥ ለምእመናንም ፥ ለአገልጋዮችም ትልቅ ኪሳራ ነው ።



2ኛ/ የቦታ ርቀት :-

በቁጥር በጣም ያደገች ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ራሳቸዉን መጠየቅ ከሚገባቸው ጥያቄዎች አንዱ የቤተ ክርስቲያኗ ምእመናን ምን ያህል ርቀት እየተጓዙ እንደሚመጡ ነው ።

ይህ ጉዳይ መጠየቅ ያለበትና ትኩረት እንዲሰጠው የሚያስፈልግ ጉዳይ ነው ። ይህ ነገር አንደኛ ከገንዘብ አንጻር ፥ ሁለተኛ ከጊዜ አንጻር ፥ ሶስተኛ ከአደጋ አንጻር መተያየት ያለበት ነገር ነው ።

ሕዝባችን የገንዘብ ችግር ያለበት ሕዝብ ነው ። ይህ ችግር በሁሉም ዘንድ የታወቀ ችግር ስለሆነ ማተት አያስፈልግም ።

ምእመናን ራቅ ካለ ቦታ እየተጓዙ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲመጡ ለባቡር ፥ ለአውቶቡስ ፥ ለታክሲ ፥ ለጋሪ የሚከፈል የገንዘብ ወጭ ይኖርባቸዋል ። እነዚህ ምእመናን በየጊዜው ወደ ቤተ ክርስቲያናቸው እየሄዱ መባረክና ማገልገል እየፈለጉ ከገንዘብ እጦት የተነሳ አልፎ አልፎ ወይም ጨርሶ ከቤተ ክርስቲያናቸው ለምቅረት ሊገደዱ ይችላሉ ። የቦታ ርቀት የሚያስከትለው ችግር የገንዘብ ችግር ብቻ አይደለም ። የጊዜም ችግር አለው ። ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሚያጠፉት ጊዜ ሌላ በተጨማሪ ለመሄጃና ለመመለሻ የሚያጠፉት ጊዜ ቀላል አይሆንም ። ሁል ጊዜ ባቡርን ፥ አውቶቡስን ፥ ታክሲን ፥ ጋሪን ጠብቆ ወይም በእግር ተጉዞ

መሄድ አሰልቺና አድካሚ ነው ።

የቦታ ርቀት በተለይም በእድሜ ለገፉ አዛዉንት ፥ የጤና ችግር ላለባቸው ምእመናን ፥ ልጆች ላላቸውና ለነፈሰጡሮች ተስፋ አስቆራጭ ይሆንባቸዋል ። ስለዚህ " ሰዉን የእግዚአብሔር ፍቅር ግድ ካለው ሁሉም ነገር ይቻላል " በማለት ብቻ ጉዳዩ በቀላሉ የሚታይ ነገር እንዳልሆነ መረዳት ያስፈልጋል ።

ከቦታ ርቀት ጋር አያይዘን ማየት ያለብን ሌላው ጉዳይ የአደጋ ጉዳይ ነው ። ቤተ ክርስቲያናቸው ሄደው ለመመለስ ብዙ ርቀት መጓዝ ያለባቸዉን ምእመናን ከሚያስፈራቸው ነገሮች አንዱ የአደጋ ጉዳይ ነው ። በተለይ ከሰዓት በኋላና ምሽት ላይ የሚካሄዱትን ስብሰባዎች ተካፍለው ወደ ቤታቸው እስኪደርሱ ድረስ የሚመሽባቸው ፥ የሚጨልምባቸው ምእመናን ይኖራሉ።

ለብዙ ሰዎች ፥ በተለይም ለሴቶች በምሽት በጨለማ መጓዝ ለልዩ ልዩ ወንበዴዎች መጋለጥን ያስከትላል ። እዉነት ነው ይህ ችግር ከቦታ ቦታ ይለያል ። ይሁን እንጂ የትም ቦታ ቢሆን ስጋትን ሳያስከትል አይቀርም ። ስለዚህ የቦታ ርቀት ለምንም የማይመች ነገር መሆኑ ታውቆ መፍትሔ እንዲፈለግለት ያስፈልጋል ።

### 3ኛ/ የምእመናን መገልገል

የኢጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የምእመናን ቁጥር በጣም እየጨመረ ሲሄድ ሊኖሩ ከሚችሉት ችግሮች መካከል አንዱ የምእመናን በቂ አገልግሎት ያለ ማግኘት ነው ።



አንደኛ ከመድረክ በሚሰጠው አገልግሎት በሚገባ ሁኔታ ሊገለገሉ አይችሉም ። ምክንያቱም በስብከቱና በአምልኮቱ ጊዜ በማያመች ሁኔታ ውጭ ዝናብ ውስጥና ጸሐይ ላይ ቆመው ስለሚሳተፉ ነው ።

ሁለተኛው ከሕዝብ ብዛት የተነሳ አገልጋዮች በምእመናን መንፈሳዊ ሕይወትና እለታዊ ኑሮ ውስጥ ሊኖሩ የሚችሉትን ችግሮች ለማወቅ አይችሉም ። ምእመናኑና አገልጋዮች በሚገባ ሊተዋወቁ አይችሉም ። ይህም ማለት አገልጋዮች ምእመናናቸውን አያውቁም ፤ ምእመናኑም አገልጋዮቻቸውን አያውቁም ። ከዚህ የተነሣ ፥ የጤና ችግር ቢፈጠር ፥ የትዳር ችግር ቢነሣ ፥ እምነታቸውን የሚጎዳ መንፈሳዊ ጥያቄ ቢያጋጥማቸው ፥ ሊላቀቁት ያልቻሉ ኃጢአት ወይም መጥፎ ሱስ ቢታገላቸው አስፈላጊውን እርዳታ ለማግኘት አይችሉም ።

በእነዚህና እነዚህን በመሳሰሉ ችግሮች ምክንያት ተስፋ ቆርጠውና ግራ ተጋብተው ከቤተ ክርስቲያን ቢቀሩ መቅረታቸውን እንኳ የሚያስተውል ሰው አይኖርም ።

የእግዚአብሔር ቃል ምእመናንንና የምእመናንን አገልጋዮች በበጎችና በበጎች ጠባቂዎች ይመስላቸዋል ። በዚህ አመለካከት በጎችና ጠባቂዎች በሚገባ ይተዋወቃሉ ( ዮሐ 10:3-5) ። ይህ መተዋወቅ ከሌለ ተገቢና አጥጋቢ አገልግሎት ለመስጠትም ለመቀበልም አይቻልም ። መተዋወቅ ከሌለ ምእመናን እንደ መንገደኞች ወይም እንደ ገበያተኞች ዝም ብለው ይተላለፋሉ ።

አገልጋዮች የምእመናንን ሁኔታ ቀረብ ብለው ሲያውቁ

ነው ለምእመናን ወቅታዊ አገልግሎት ለመስጠት የሚችሉት ። ይህ ዓይነት መቀራረብና እውቀት ሲኖር ነው የጠፋውን ፈልጎ ለመመለስ ፣የራቀውን ለማቅረብ ፣ የተሰበረውን ለመጠገን ፣ የቆሰለውን ለመፈወስ ፣ሆድ የባሰዉን ለማጽናናት ፣ የተጣመመውን ለማቅናት ፣ የወደቀውን ለማንሳትና የሐሰትን ትምህርት ለመቆጣጠር የሚቻለው ።

## 4ኛ/ የአገልጋዮች ውጥረት

በቁጥር ከመጠን በላይ ባደገው የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚኖረው ሌላ ችግር የአገልጋዮች ውጥረት ነው ። አገልጋዮች ሰማያዊ ጥሪ ያላቸው ፣ራሳቸውን ለእግዚአብሔርና ለምእመናኑ የሰጡ ፣ በታማኝነትና በትጋት የሚያገለግሉ ሊሆኑ ይችላሉ ። ለምእመናኑ መሰጠት ያለባቸውንም የአገልግሎት ዓይነቶች ሊገነዘቡ ይችላሉ ።

ነገር ግን በጊዜ እጥረትና በአገልግሎቱ ብዛት ምክንያት ሁሉንም ምእመናንን ለማዳረስ አይችሉም ። ከዚህ የተነሣ ኑሮአቸው የውጥረት ኑሮ ፣ አገልግሎታቸው የውጥረት አገልግሎትና ሕሊናቸው በወቀሳ የተሞላ ይሆናል ። ከዚህ የተነሣ የተቀደሰው አገልግሎት የሚያስጠላ ሸክምና ነፍስን የሚያስመርር ሐላፊነት እየሆነ ይሄዳል።

ቤተ ክርስቲያን ሌሎች አዳዲስ አገልጋዮችን አዘጋጅታ ብታሰልፍ እንኳ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩ ሌሎች ችግሮችም ስላሉ ለጉባኤው አጥጋቢና ወቅታዊ አገልግሎት ለመስጠት አይቻልም ። መፍትሔው ምንድነው ? መፍትሔ የሚሆነውን አሳብ በኋላ



አቀርባለሁ ።

## 5ኛ/አገልጋዮችን ማፍራት

በቁጥር በጣም በበዛና ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ችግሮች ባሉበት የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አገልጋዮችን ማፍራት አስቸጋሪ ይሆናል ። አንደኛ በምእመናን መካከል ማን ማን እንደሆነ ለማወቅ ስለሚያስቸግር የሰዎችን የጸጋ ስጦታና ጥሪ ማወቅ አይቻልም ። ሙከራ ቢደረግም እንኳ ለሁሉም የአገልግሎት በር ማግኘት አይቻልም ። የሰውን የጸጋ ስጦታ ካላወቁ አሰልጥኖ ፣ አዘጋጅቶ ለአገልግሎት ማሰለፍ አስቸጋሪ ይሆናል ።

ሁለተኛ አሰልጥኖም ለማሰለፍ ሙከራ ቢደረግም እንኳ ለሁሉም የአገልግሎት ቦታ ማግኘት አይቻልም ። ለምሳሌ የእረኝነት ጥሪ ያላቸው ፣ የሽምግልና ጸጋ ያላቸው ፣ የማስተማር ጸጋ ያላቸው ፣ እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ ምእመናን የአገልግሎት ቦታ አግኝተው ሁሉም ጸጋቸውን ለእግዚአብሔር ሕዝብ ለማበርከት አይችሉም ።

ከዚህ የተነሳ በልዩ ልዩ ጸጋዎች የተሞሉ ምእመናን ዘመናት እንዲሁ በከንቱ ያልፋል ። ጸጋዎቻቸውም የአጨዳ ጊዜው እንዳለፈበት የስንዴ መከር ምንም ጥቅም ሳይሰጡ ባክነው ይቀራሉ ። ከዚህ ሁኔታ የሚጠቀመው ሰይጣን ብቻ ነው ። ለእግዚአብሔርና ለእግዚአብሔር ሕዝብ ግን ታላቅ ኪሳራ ነው ።

ስለወንጌሉ ሥራ ሙሉ እውቀት ያለው ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል 9:37-38 “ መከሩ ብዙ ነው ፤ የመከሩ ሠራተኞች

ግን ጥቂቶች ናቸው ። እንግዲህ ተጨማሪ ሠራተኞችን ወደ መከሩ ሥራ እንዲልክ የመከሩን ጌታ ለምኑት ” ሲል ያዘዘው ሰማያዊ ትእዛዝ ዛሬም ያልተሻረ መሆኑን መገንዘብ አለብን ። ዘሩን ለመዝራትና መከሩን ለመሰብሰብ የተላኩትን የንጉሡን ሠራተኞች ተቀብሎ ማሰለፍ የቤተ ክርስቲያን ግዴታና እድል ፈንታ ነው ። ዘሩን ለመዝራትና መከሩን ለመሰብሰብ የተሰለፉትን ሠራተኞች አይቶ ዝም ማለት ወይም ያለ አግባብ ማስጠበቅ በመከሩ ባለቤት ዘንድ ያስጠይቃል ።

6ኛ/ የራእይ ጥራት

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩ ችግሮች ባሉበት ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የራእይም ችግር ይኖራል ። ለምን ይኖራል ?

አንደኛ አገልጋዮች በትልቅ ውጥረትና በተዋከበ አእምሮ ስለሚያገለግሉ ጊዜ አግኝተው በጥሞና አገልግሎታቸውን መመዘን ያስቸግራቸዋል ። በዚህ በኩል ሲያቃኑት በዚያ በኩል ይደፋባቸዋል ። ይህን ሲሉት ሌላው ይቀራል ። በዚህ በኩል ሲሳካ በሌላው በኩል ይበላሽባቸዋል ።ኑሮውም የሩጫ ኑሮ ፣ አገልግሎቱም የሩጫ አገልግሎት ይሆንባቸዋል ።

ሁለተኛ ከአገልግሎቱ ስፋትና ከችግሩ ብዛት የተነሣ ነገሮች ይወሳሰባሉ ። ውሉ እንደጠፋበትና ድሩ እንደተወሳሰበበት ሸማኔ ግራ ይጋባሉ ። የጠራ ራእይ አይኖርም ። በየእለቱ ተነስቶ መሮጥ አይቀርም ። ነገር ግን ግብ ያለው ሩጫ አይሮጥም ።

ይህን አሳብ በምሳሌ ለመግለጥ የሚችል በመጽሐፍ ያነበብሁት



ታሪክ ታወሰኝ ። ታሪኩ ከዚህ እንደሚከተለው ነው ። አንድ የንግድ አውሮፕላን ነጂ ብዙ ሰዎችን አሳፍሮ በአየር ላይ ጉዞ ጀመረ ። በዚህ ጉዞ ላይ እያለ የአውሮፕላኑ ሞተርና አውሮፕላኑ የሚሄድበትን አቅጣጫ የሚያመለክት መሳሪያ ተበላሹበት ።

ያጋጠመውን ችግር ለተሳፋሪዎቹ ማስታወቅና እንዳይረበሹ ማበረታታት ነበረበት ። የተበላሸው ሞተር እንደገና እንዲሠራ ለማድረግ ብዙ ከታገለ በኋላ ቀንቶት ሞተሩ መሥራት ጀመረ ። ይሁን እንጂ የአውሮፕላኑን አቅጣጫ የሚያመለክተዉን መሳሪያ መልሶ እንዲሠራ ለማድረግ አልቻለም ።

አሁንም የአዉሮፕላኑን ሁኔታ ለተሳፋሪዎቹ ማስታወቅ ስለነበረበት ከዚህ ቀጥሎ ባለው አገላለጥ አስታወቃቸው ፡ “ ክቡራንና ክቡራት በአንድ በኩል መልካም ዜና ፣ በሌላ በኩል ደግሞ መጥፎ ዜና አለኝ ። መልካሙ ዜና ፣ የአውሮፕላኑ ሞተር በሚገባ መሥራት ጀምሮአል ። መጥፎው ዜና ፣ የአውሮፕላኑን አቅጣጫ የሚያሳየው መሣሪያ እንደገና እንዲሠራ ለማድረግ አልተቻለም ። ይህም ማለት አዉሮፕላናችን በሚገባ እየበረረ ነው ያለው ። ነገር ግን ወዴት እየበረርን እንዳለን አቅጣጫችንን አናውቅም ” ።

ወደ አዲስ አበባ እንዲወስደን የተሳፈርነው አውሮፕላን አቅጣጫውን በመሳት ወደ ህንድ አገር ቢወስደን ኪሳራ ነው እንጂ ትርፍ አይደለም ። የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት አቅጣጫና ግብ ያለው መሆን አለበት ። በተጨማሪ አቅጣጫችንን ያለ መልቀቃችንና ከግባችን መድረሳችንን ለመመዘን መቻል አለብን ። ገበሬ እንኳን ስንት ቁና ጤፍ እንደዘራና ከዚያ ዘር ስንት ቁና እንዳመረተ ያውቃል ።

## 7ኛ/ አመራርና አስተዳደር

እስከ አሁን እንደ ተመለከትነው በትልቅ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ምእመናን ፥ ሰፊ አገልግሎትና ብዙ ችግሮች ይገኛሉ ። እነዚህ ሁኔታዎች የቤተ ክርስቲያኑን አመራርና አስተዳደር ከባድና አስቸጋሪ ያደርጋሉ ።

አንደኛ ችግሮች እንዳይፈጠሩ በቅድሚያ መቆጣጠር ቀላል አይሆንም ። የሚፈጠሩም ችግሮች ብዙዎች ይሆናሉ ። ብዛት ብቻ ሳይሆን ችግሮቹም የተለያዩ ችግሮች ይሆናሉ ።

ሁለተኛ ችግሮቹ መፈጠራቸው የሚታወቀው ሥር ከሰደዱና የጉባኤዉን ሕይወትና የቤተ ክርስቲያኑን አገልግሎት ከበከሉ ፥ ከጎዱና ትልቅ ቀውስ ከፈጠሩ በኋላ ነው ።

ሶስተኛ ችግሮቹ የተለያዩ ችግሮች እንደመሆናቸው መጠን ለያንዳንዱ ችግር መፍትሔ ማግኘት ቀላል አይሆንም ። አገልጋዮች በተለይም መሪዎች ቤተ ክርስቲያ ወደ ፊት እንድትራመድ ከማድረግ ይልቅ የተፈጠሩትን ልዩ ልዩ ችግሮች ለማስተካከል ሲዳክሙ ጊዜአቸው በከንቱ ያልቃል ። ይህ ደግሞ የቤተ ክርስቲያኗን አገልግሎት ፥ ጤናና እድገት እጅግ ያቃውሳል ።

እስከ አሁን ድረስ የተዘረዘሩት እነዚህ ልዩ ልዩ ጠንቆች ቤተ ክርስቲያኗ እስከ አሁን የደረሰችበትን እድገት የሚያበላሹና ወደፊትም እንዳታድግ እንቅፋት የሚሆኑ ጉልህ ችግሮች ለመሆናቸው ብዙ አብያተ ክርስቲያናት በልምምድ ደርሰውባቸዋል ። ታዲያ



መፍትሔው ምንድነው ? መፍትሔውን ከዚህ ቀጥዬ አቀርባለሁ።

### መፍትሔው :-

ከሁሉ አስቀድሞ እነዚህ ወደዚች ቤተ ክርስቲያን እየመጡ ጌታን የሚያመልኩ ምእመናን የሚኖሩባቸውን ሰፈሮች ማጥናት ። ከዚህ ጥናት ቀጥሎ የቤተ ክርስቲያኗን ምእመናን ጠቅላላ ቁጥር ወይም ብዛት ምን ያህል እንደሆነ ማወቅ ።

እነዚህ ሁለት ጥናቶች በሚገባ ከተጠናቀቁ በኋላ የቤተ ክርስቲያኗን ምእመናን ስንት ቦታ መከፈል እንደሚያስፈልግ መወሰን ። በዚህ ውሳኔ መሠረት አዳራሾች መከራየት ወይም መኮናተር ። አቅም ከፈቀደም የራስ የሆኑ አዳራሾችን ማዘጋጀት።

በዚህ መሠረት በየሰፈሩ የጉባኤዎች አገልግሎት ከመጀመሩ አስቀድሞ ለያንዳንዱ ጉባኤ ሽማግሌዎች ( ካሉ እረኞችም ጨምር ) መመደብ ። በተጨማሪም ለእያንዳንዱ ጉባኤ ወንጌላዊን ወይም ወንጌላውያንን መመደብ ። ለእያንዳንዱ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የተሟላ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉትን ልዩ ልዩ የአገልግሎት ቡድኖችንንም መመደብ ። ለምሳሌ ያህል እንደ ዲያቆናት ፥ መዘምራን ፥ የክትትል ትምህርት አስተማሪዎች ፥ የማጽናናት አገልግሎት ቡድን ወዘተ ማለቴ ነው ።

እያንዳንዱ ጉባኤ ራሱን በራሱ ለመምራትና ለማስተዳደር እንዲችል ማድረግ ። በወጭም ረገድ ቢሆን እያንዳንዱ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ራሱን ችሎ አገልግሎቱን እንዲያካሂድ ማድረግ ። ጉባኤው አገልግሎቱን ሲጀምር በገንዘብ ራሱን መርዳት የማይችል

ሆኖ ከታየ ራሱን እስኪችል ድረስ መርዳት አስፈላጊ ነው ።

አንድነትን ለመጠበቅና በሕብረት አብሮ ለማገልገል እንዲረዳ ኮሚቴ ወይም የቀጠና መሪዎች መመደብ ። እነዚህ የቀጠና መሪዎች ወይም የኮሚቴ አባላት ከእያንዳንዱ ጉባኤ መሪዎች የተውጣጡ መሆን አለባቸው ። የዚህ ዓይነቱ ሕብረት ለብዙ ነገሮች ይጠቅማል ።

1ኛ/የጉባኤዎቹ ( የምእመናን ) መንፈሳዊ አንድነት እንዳይቋረጥ ይረዳል ።

2ኛ/ የሐሰት ትምህርት ጉባኤዎችን እንዳይበክል ለምቆጣጠር ዓይነተኛ ዘዴ ይሆናል ።

3ኛ/ ነባሮችንም ሆነ የወደፊት አገልጋዮችን በሕብረት ለማሰልጠን ፣ ለማጎልመስና ለማሳለፍ ይጠቅማል ።

4ኛ/ እንደ አስፈላጊነቱ ለምእመናን የአንድነት ኮንፈራሶችን ለማዘጋጀት ጠቃሚ ዘዴ ይሆናል ።

5ኛ/ አገልግሎትን በማስተባበር ወንጌል ያልደረሰዉን የአካባቢውን ሕዝብ በወንጌል ለመድረስ ይጠቅማል ።

6ኛ/ የአገልግሎትን ራእይ ፣የአሠራርንና የአደራረግን ዘዴ አብሮ ለመካፈል ያስችላል ።

7ኛ/ አገልጋዮችን ፣ መድረኮችንና ቁሳቁሳዉያን ነገሮችን በሕብረት በመካፈል ለመረዳዳት ይጠቅማል ።

አባላት በቁጥር በጣም የበዙበትን የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በዚህ ዓይነት መከፈል ለብዙነገሮች ጠቃሚ ይሆናል ።

1ኛ/ አባላት በሚገባ ይገለገላሉ ። በመንፈሳዊ ሕይወታቸውና በአገልግሎታቸው እጅግ ይታነጻሉ ። የዳኑትም በጌታ ቤት ተተክለው



ይቀራሉ ።

2ኛ/አገልጋዮች ከውጥረት ነፃ ይወጣሉ ። ስለሆነም ጸጋቸውን እያሳደጉ አገልግሎታቸውን በደስታና በጠራ ራእይ ያከናውናሉ።

3ኛ/ምእመናኑን ያስቸግር የነበረው የቦታ ርቀት ችግር ይቃለላል ። በየአካባቢያቸው ተዝናንተው ጌታን ያመልካሉ ፣ ያገለግላሉም ።

4ኛ/ከቦታው ርቀት ጋር የተያያዙ የገንዘብና ( የመጓጓዣ ) የአደጋ ችግሮች ይቃለላሉ ። በጊዜ ወደ ቤታቸው ለመግባት ስለሚችሉ ለወንበዴዎች አይጋለጡም ።

5ኛ/የአስተዳደርና የአመራር ችግሮች በብዙ ይቃለላሉ ። አገልግሎቱ ራእይ ፣ ጥራትና ቅልጥፍና ያለው አገልግሎት ይሆናል ።

6ኛ/ቤተ ክርስቲያኒቷ ብዙ አገልጋቶችን ለማፍራት ትችላለች ። እግዚአብሔር በሰጣቸው ጸጋ መሠረት ብዙ ምእመናን ለአገልግሎት ይሰለፋሉ ። ተቀምጠው ተመልካቾች የነበሩት ሰዎች አሁን በተዘረጉት ልዩ ልዩ የአገልግሎት ዘርፎች ተሰልፈው ለእግዚአብሔር ይዋጋሉ።

7ኛ/በአጠቃላይ ይህ ዓይነቱ አሠራር ለቤተ ክርስቲያን እድገት ዓይነተኛ ዘዴ ይሆናል ። ዘዴው በብዙ አገሮች የተፈተነ ጠቃሚ ዘዴ ሆኖ ተገኝቷል ። ከእድገቱ ዘዴዎች መካከል አንዱ ይህ ነው ።

የመፍትሔው እንቅፋት :-

በዚህ መፍትሔ እንዳንጠቀም እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ ሁለት ነገሮች አሉ ። አስተዋዮች ከሆን እነዚህን ሁለት ነገሮች ማሸነፍ እንችላለን ።

1ኛ/ ስሜት :-

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በቁጥር በጣም በዝቶ መከፈል የሚያስፈልግበት ደረጃ ለመድረስ በርካታ ዓመታት ይጠይቃል ። በእነዚህ ዓመታት ውስጥ ምእመናን ብዙ የጋራ ልምምዶችንና ትዝታዎችን ያከማቻሉ ። ጥቂት የነበሩ ምእመናን ዛሬ በቁጥር በዝተው ከዚህ ደርሰዋል ። ይህ የጋራቸው ልምምድ ነው ።

በተቃዋሚዎች ምክንያት አብረው መጠላታቸው ፣ አብረው መሰደባቸው ፣ አብረው መሰደዳቸው ፣ አብረው ብዙ መከራ መቀበላቸው ይታወሳቸዋል ።

በዚሁ መጠን አብረው ከእግዚአብሔር የተቀበሉትን በረከት ፣ በአንድነት የታነጹትን መታነጽ ፣ አብረው ጸልየው መልስ ያገኙበትን ጸሎት ፣ አብረው በእውነትና በመንፈስ አምላካቸውን ያመለኩበትን አምልኮታቸውን ሁሉ ያስታውሳሉ ። በፍቅርና " እኛ " ፣ " የእኛ " በሚሉት ማንነት እንደ ቤተሰብ ተሳስረዋል ። " እገሊት የቤተ ክርስቲያናችን አባል ናት " ፣ " እገሌ የቤተ ክርስቲያናችን አባል ነው " ሲሉ ኖረዋል ።

ስለዚህ አሁን በየሰፈሩ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኖች ሆነን



ጌታን እናምልክ ፣ ጌታን እናገልግል ፣ ነፍሳትን እንድረስ ሲባል የማይዋጥ ጉዳይ ሆኖ ይታያቸዋል ።

አንድነታቸው ፈራርሶ የሚበታተኑ ይመስላቸዋል ። " እኛ " ፣ " የእኛ " የሚለው ምንነታቸው የሚሰረዝ ይመስላቸዋል ። በአጭሩ ስሜታቸውን ማሸነፍ ስለሚያቅታቸው እንዲሁ አሁን ባሉበት ሁኔታ መቆየትን ይመርጣሉ ።

እንደ እውነቱ ከሆነ ስሜታችንን ማሸነፍ አቅቶን ነው እንጂ ፣ በየሰፈሩ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በመሆን ጌታን ማምለክና ማገልገል አንድነታችንን አፈራርሶ አይበታትነንም ።

ከእልፍ አእላፋት ቅዱሳን ጋር ፣ በአዲሲቱ እየሩሳሌም ፣ በተቀደሰው አምላካችን ዙፋን ፊት ተከማችተን ፣ በአንድነት ቤዛችንን ለዘላለም ስናመልክ እንኖራለን ። ከነገድና ከቋንቋ ፣ ከሰሜንና ከደቡብ ፣ከምስራቅና ከምዕራብ በበጉ ደም የተዋጀን ሁሉ ለአባታችን የምስጋናን የውዳሴን መስዋእት እያቀረብን እንደ አንድ ጉባኤ የምንኖርበት ጊዜ ይመጣል ።

ዛሬ ግን የሥራ ቀን ነው ። ዛሬ ነፍሳትን በየአራቱ ማእዘናት ፣ በየሰፈሩና በየመንገዱ ለጌታ የምንመልስበት ቀን ነው ፣ ስለዚህ ስሜታችንን እናሸንፍ ። አርቀን እንመልከት ። እንብዛ ። እንስፋፋ ። ምድርንም እንሙላ ። ከተሞችን ፣ መንደሮችን ፣ ገጠሮችን ሁሉ በጌታችን ወንጌል እንዉረር ።

2ኛ/ ስም

ምናልባት ቤተ ክርስቲያኑ በከተማው ካሉት አብያተ ክርስቲያናት መካከል በአባላት ብዛት ከፍተኛና የታወቀ ቤተ ክርስቲያን ከሆነ ፤ የስም ጉዳይ ችግር ሊሆን ይችላል ።

“ የእኛ ቤተ ርስቲያን በከተማው ካሉት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በአባላት ብዛት አንደኛ ነው ” ። “ እኛ እንበልጣለን ” የሚሉ አመለካከቶች ካሉ ለቀረበው መፍትሔና ለቤተ ክርስቲያን እድገት እንቅፋት መሆን ይችላል ። የስም ጉዳይ ጣኦት ሊሆንብን ይችላል ማለት ነው ።

ከአፋችን አውጥተን እኔ ባስቀመጥሁት አረፍተ ነገር አንናገርም ይሆናል ። ይሁን እንጂ ይህ አሳብ ፣ ይህ አመለካከት በልባችን ካለ ፣ በልብ ዙፋን ላይ የተቀመጠ ጣኦት ይሆናል ። ነገር ግን ጣኦቱ መነሳት አለበት ።

“ እንዲህም አሉ ፣ ኑ አንድ ከተማ እንመሥርት ፤ በዚያም ጫፉ እስከ ሰማይ የሚደርስ ግንብ እንሥራ ፤ በዚህ ዓይነት በምድር ላይ ከመበታተናችን በፊት ስማችንን እናስጠራ ” ( ዘፍ 11:4 ) ።

የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የምትኖረው ለራስ ስም አይደለም ። ቤተ ክርስቲያን የምትኖረው ለሞተላት ጌታ ኢየሱስ ነው ። ለራሷ ታዋቂነት ሳይሆን ለጠፉት ነፍሳት ደህንነትና ለእግዚአብሔር ክብር ትኖራለች ። ለራሷ ስም ፣ ለራሷ ዝናና ታዋቂነት የምትኖር ቤተ ክርስቲያን ተልእኮዋን በሚገባ ሁኔታ ያልተረዳች ቤተ ክርስቲያን ናት ። ስለዚህ የስም ጉዳይ ችግር እንዲሆንብን አያስፈልግም።



## አዲስ ጉባኤን በአካባቢ በመጀመር

ቤተ ክርስቲያን የምታድግበት ሶስተኛው ዘዴ አዲስ ጉባኤ በመጀመር ነው ። አዲስ ጉባኤን ለመጀመር ከመነሳት በፊት መታሰብ ያለባቸው ነገሮች አሉ ።

1ኛ/ ከሁሉ አስቀድሞ መታሰብ ያለበት ዓላማው በሁሉም ነገር ራሱን የቻለ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለማቋቋም መሆን አለበት ። ለሁልጊዜ ጥገኛ ሆኖ የሚቀር አገልግሎት እንዳይሆን መጠንቀቅ ያስፈልጋል ።

2ኛ/አገልግሎቱ የሚጀመረው በከተማ ውስጥ ከሆነ ከተማው ወደፊት በየትኛው አቅጣጫ እያደገ እንደሚሄድ በሚገባ ማወቅ ያስፈልጋል ። ወደፊት ሕዝብ እየበዛበት በሚሄድ ሰፈር መጀመር የቤተ ክርስቲያናን የወደፊት አገልግሎት ፍሬአማ ያደርገዋል ። ብዙ ነፍሳትን ለመድረስ ያስችላል ማለት ነው ። ስለዚህ አስቀድሞ ይህን ጥናት ማድረግ አስፈላጊ ነው ።

3ኛ/ ይህን አገልግሎት የምትጀምር ቤተ ክርስቲያን ፣ መንፈሳዊ ብስለት ያላቸውን ፣ የነፍሳት ፍቅር የሚታይባቸውንና ጸጋ ያለባቸውን ሰባት ሰዎች ኮሚቴ አድርጋ መመደብ ። የዚህ ኮሚቴ አባላት ሆነው አገልግሎቱን የሚያካሂዱ አንድ ሽማግሌና ሁለት ወንጌላውያን መመደብ አለባቸው ።

4ኛ/ከዚህ በፊት ሕይወትን የሚለውጥ የወንጌል አገልግሎት ያልደረሰበትን ሰፈር ለይቶ ማወቅ ። ፍሬአማ አገልግሎት እየተካሄደ

ያለበት ቦታ ሄዶ ከመጀመር ሕይወትን የሚለውጥ የወንጌል አገልግሎት የሌለበት ሰፈር መጀመር ለሁሉም ነገር ጠቃሚና ትክክለኛ ይሆናል።

ሌላ ጤነኛና ፍሬአማ የወንጌል አገልግሎት የሚካሄድበት ቢሆንም እንኳ የሰፈሩ ሕዝብ ብዙ ከሆነ ፥ ወይም ከተማው ወደፊት እያደገ የሚሄድ ከሆነ አዲስ አገልግሎት እንዳይጀመር የሚከለክል ነገር የለም ።

ከዚህ በላይ ለተጠቀሱት አስፈላጊ ነገሮች ትኩረት ከተሰጠ በኋላ አገልግሎቱን ለመጀመር እርምጃ ይወሰዳል ። እንዴት ነው የሚጀመረው ? በሁለት መንገዶች ለመጀመር ይቻላል ።

1ኛ/ አገልግሎት ሊጀመርበት በሚታሰበው ሰፈር አማኝ ወይም አማኞች እንዳሉና እንደሌሉ ማጥናት ። አማኝ/አማኞች ካሉ ከእነዚህ አማኞች ጋር ተገናኝቶ ዓላማውን ማስረዳት ። ከእነዚህ አማኞች ጋር እየጸለዩ በሰፈሩ የመሰብሰቢያ አዳራሽ መከራየት ወይም መኮናተር ። ስለሚጀመረው አገልግሎት በጾምና በጸሎት በእግዚአብሔር ፊት ከቆዩ በኋላ አገልግሎቱን በእምነት መጀመር ።

2ኛ/ በሰፈሩ አማኞች ባይኖሩ አዳራሽ ፈልጎ መከራየት ወይም መኮናተር ። በጾምና በጸሎት ጊዜ ወስዶ በእግዚአብሔር ፊት ከቆዩ በኋላ ከነባሩ ቤተ ክርስቲያን አስር የሚሆኑትን ምእመናን መውሰድ ። ከአገልግሎቱ ኮሚቴ ጋር አስራ ሰባት ይሆናሉ ማለት ነው ።

በእነዚህ አስራ ሰባት ምእመናን ተሳታፊነት አገልግሎቱን



መጀመር ። አገልግሎቱ ሥር ሰዶ ከሰፈሩ ነፍሳት ወደ ጌታ መምጣት እስኪጀምሩ ድረስ እነዚህ አስሩ ምእመናን ያለ ማቋረጥ በዚህ አዲስ ሰፈር ሰባቱን የአገልግሎት የኮሚቴ አባላት መርዳት አለባቸው ።

በእነዚህ ሁለት መንገዶች ለሚጀመረው የአዲስ ሰፈር አገልግሎት መዘምራንንም በቋሚ ደረጃ መመደብ ጥሩ ውጤት ይሰጣል ። የመዘምራኑ ቁጥር አነስተኛም ቢሆን ጥሩ የዝማሬ አገልግሎት ለመስጠት እስከቻሉ ድረስ የቁጥሩ ጉዳይ አሳሳቢ መሆን የለበትም ።

አዲሱ አገልግሎት በሚገባ ተመስርቶ ራሱን በራሱ መምራትና ማስተዳደር እስኪችል ድረስ ነባሩ ቤተ ክርስቲያን በገንዘብ ፥ በአመራር ፥ በአገልግሎትና በጸሎት አስፈላጊዉን እርዳታ ማደረግ አለበት ።

በዚህ ዓይነት አዲሱ ጉባኤ የራሱ ሽማግሌዎች ፥ እረኛ ፥ ወንጌላዊ ፥ ወዘተ ያለው ጉባኤ በመሆን የአጥቢያውን ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ለማካሄድ ይበቃል ማለት ነው ። በዚህን ጊዜ በገንዘብም የራሱን የአጥቢያ አገልግሎት ለማካሄድ የሚችል ጉባኤ መሆን ይገባዋል ። ይህ ሶስተኛው የቤተ ክርስቲያን የእድገት ዘዴ ነው ።

## አዲስ ጉባኤ ራቅ ብሎ በመጀመር

አራተኛው የቤተ ክርስቲያን የእድገት ዘዴ አዲስ ጉባኤን ራቅ ብሎ መጀመር ነው ። ነባሩ ቤተ ክርስቲያን ፥ ራቅ ብለው

የሚገኙትን ፥ ወንጌል ያልደረሰባቸውን ቦታዎች ማጥናት ። ይህን ጉዳይ የሚያጠኑትን አምስት ሰዎች በኮሚቴ መልክ መመደብ።

ኮሚቴው አንድ ሽማግሌ ፥ አንድ ወንጌላዊ ፥ ሶስት ለዚህ ጥናት ብቃት ያላቸው ምእመናን ያሉበት ቢሆን ጥሩ ውጤት ያመጣል ።

ጥናቱ ከተደረገ በኋላ ነባሩ ቤተ ክርስቲያን በጥናቱ መሠረት ወደ ተወሰነው ቦታ አንድ በሙሉ ጊዜ የሚያገለግል ወንጌላዊ በቋሚነት መላክ ። ወንጌላዊዉን በገንዘብም ፥ በአሳብም ፥ በጸሎትም መርዳት ።

ወንጌላዊው ቤት ተከራይቶ አካባቢዉን በሚገባ ከተላመደው በኋላ በቤቱ ስብሰባ መጀመር ይችላል ። በዚህ ሁኔታ አገልግሎቱ ከተጀመር በኋላ አዳራሽ ተከራይቶ የወንጌሉን ስርጭት በሰፊው መጀመር ። በዚህን ጊዜ ነበሩ ቤተ ክርስቲያን ይህን አዲስ አገልግሎት በቅርቡ እየተከታተለ አገልግሎቱ ሥር እንዲሰድና በሚገባ እንዲመሠረት ማድረግ አለበት ።

አልፎ አልፎ አገልጋዮችን በመላክ ወንጌላዊውን ማበረታታት ፥ መርዳትና ማጽናናት አስፈላጊ ነው ። ከወንጌላዊው ጋር በመመካከር አልፎ አልፎ ኮንፈራንስ ማዘጋጀት የአገልግሎቱን እድገት ያፋጥናል ። ለኮንፈረንሱ የሚያስፈልገዉን ወጭ ፥ የሰው ጉልበት ፥ መዘምራን ፥ ጌታን ለሚቀበሉ ሰዎች ምክር የሚሰጡትን አገልጋዮች ማበርከት አስፈላጊ ነው ።

የነባሩ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች በየጊዜው ተራ በተራ እየሄዱ ከወንጌላዊው ጋር በመጸለይ የሞራል ድጋፍ ፥ የምክር



፥ የማጽናናት አገልግሎትና ለችግሮች መፍትሔ የማግኘት አገልግሎት መስጠት ጥሩ ይሆናል ።

አሁንም ዋና ዓላማው በዚህ ቦታ የራሱ ሽማግሌዎች ፥ እረኛ ፥ ወንጌላዊና ሌሎችም አስፈላጊ አገልጋዮች ያሉት ጉባኤ ለመመሥረት መሆኑ መዘንጋት የለበትም ። በተጨማሪም በገንዘብ ፥ በአስተዳደር ፥ በአገልግሎትና በሌሎች አስፈላጊ ነገሮች ሁሉ ራሱን የቻለ ጉባኤ ለመፍጠር መሆኑን ሁል ጊዜ ማሰብ አስፈላጊ ነው ።

## በሞግዚትነት በማሳደግ

አምስተኛው የቤተ ክርስቲያን እድገት ዘዴ የተጀመረ ፥ ነገር ግን ሙሉ እርዳታ የሚያስፈልገውን አገልግሎት በመርዳት ነው ። እንደዚህ ዓይነቱ አገልግሎት የሚያስፈልጉት እርዳታዎች እንደ ቦታውና እንደ ጀማሪዎቹ ሁኔታ የሚወሰን ነው ።

በቅድሚያ መደረግ ያለበት ነገር የአገልግሎቱን ሁኔታና የጀማሪዎቹን መንፈሳዊ አቋም ማጥናት ነው ። አጀማመሩ የእግዚአብሔርን ቃል የማይቃረን ፥ የጀማሪው እምነትና ሕይወት በእግዚአብሔር ቃል የተደገፈ ፥ ቢበዛም ቢያንስም አሁን እየተሰጠ ያለው አገልግሎት እንደ እግዚአብሔር ቃል የሚሰጥ መሆኑ መጠናትና መታወቅ ፥ በእግዚአብሔር ቃል መመሥረት አለበት ።

አስቀድሞ እነዚህን ነገሮች ማወቅ ለብዙ ነገሮች ይጠቅማል

1ኛ/ አገልግሎቱን በሞግዚትነት ለመርዳትና ለማሳደግ የተነሳው ቤተ ክርስቲያን የተሳሳተ ጅማሬ ፣ የተሳሳተ እምነት ፣ የተሳሳተ ትምህርትና የተሳሳቱ ሰዎች ያሉበትን አገልግት በማቀፍ ስሙንና አገልግሎቱን እንዳያስነቅፍ ይረዳል ።

2ኛ/ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ችግሮች ባሉት አገልግሎት ላይ ዘለቄታና መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ አገልግሎት ለመመስረት አይቻልም ። ስለሆነም ዘለቄታ ያለው አገልግሎት ለማቅረብ ከመሞከር አስቀድሞ መሠረቱን አሁኑኑ ማስተካከልና ማቃናት አስፈላጊ ነው ።

ሁሉም ነገር ከተስተካከለ በኋላ አገልግሎቱን መደገፍ መጀመር በሙሉ ጊዜ የሚያገለግል አገልጋይ ከሌለው አገልግሎቱን በሙሉ ጊዜ የሚንከባከብ አገልጋይ መስጠት ።

የገንዘብ እርዳታ የሚያስፈልግ ከሆነ በተቻለ መጠን መርዳት ። እልፎ እልፎ ኮንፈራንስ ማዘጋጀት ። ኮንፈራንስ ለማዘጋጀት እንዲችሉ በቅርቡ እየተከታተሉ በአገልጋዮች ፣ በአመራር ፣ በአሠራር ፣ መዘምራንን በመላክ ወዘተ መርዳት ።

በጸሎት ፣ የሞራል ድጋፍ በመስጠት ፣ በምክር ፣ ችግሮችን አብሮ በመፍታት በአጠገባቸው መሰለፍ ያስፈልጋል ።

አሁንም ዓላማው ይህ ጉባኤ የራሱ ሽማግሌዎች ፣ እርኛ ፣ ወንጌላዊ ፣ ወዘተ ያሉት የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እንዲሆን መሆኑ መዘንጋት የለበትም ። በዚህ ሁኔታ የራሱ አመራር ፣ የራሱ አስተዳደርና የራሱ አገልግሎት ያለው የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ለመሆን ይበቃል ማለት ነው ።



በሞግዚትነት የሚረዳ አገልግሎት በተቻለ መጠን ከሞግዚትነት ወጥቶ ራሱን እንዲችል ለማድረግ መጣር ነው እንጂ በሞግዚትነት ለረጅም ጊዜ እንዲቀይ ያለማድረግ አስፈላጊ ነው ።

የቤተ ክርስቲያን እድገት የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ። ቤተ ክርስቲያን ልታድግ ከምትችልባቸው መንገዶች ወይም ዘዴዎች አንዳንዶቹን ጠቅሻለሁ ። ሌሎችም ዘዴዎች ቢኖሩ እንደ ጊዜውና እንደ አካባቢው ሁኔታ ታይቶ ሥራ ላይ ማዋል ይቻላል ።

ስለዚህ ለእድገት መጸለይና ለእድገት መሥራት አለብን ። “ ቀን ሆኖ ሳለ የላከኝን ሥራ መሥራት አለብኝ ፣ ማንም ሰው ሊሠራ የማይችልበት ሌሊት ይመጣል ” ( ዮሐ 9:4 ) የሚለው የጌታ ቃል ሁልጊዜ ሊያነቃን ይገባል ። ጊዜው ካለፈ በኋላ ወደ ኋላ ተመልክተን የምንጸጸትበት ነገር እንዳይኖር ዘወትር ማሰብ አለብን ። “ ቢያንስ ቢያንስ እንደዚህ ለማድረግ ፣ እንደዚያ ለማድረግ እንችል ነበር እኮ ” በማለት የምንጸጸትበት ፣ የጠፋ መልካም እድል እንዳኖር በንቃት እናገልግል ።

# ምዕራፍ 5

## የምእመናንን መንፈሳዊ ሕይወት ማነጽ

የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ ክፍል የሆነዉን አንዱን መሠረታዊ ነገር ተመልክተናል ። ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር መመለስ ነው።

ከዚህ ቀጥሎ ፤ የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ ክፍል የሆነዉን ሁለተኛዉን መሠረታዊ ነገር እንመለከታለን ። ይህም መሠረታዊ ነገር የምእመናንን መንፈሳዊ ሕይወት ማነጽ ነው ።

ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር መመለስ ብቻ በቂ አይደለም ። ነገር ግን ንስሐ በመግባት ኃጢአታቸዉን ተናዝዘው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው የተቀበሉትን ሰዎች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ ማድረግ አስፈላጊ ነው ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያንን ተልእኮ ትእዛዝ ለደቀመዛሙርቱ ሲሰጥ እንዲህ አለ ፤ “ .....ያዘዝሁአችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀመዛሙርቴ አድርጉአቸው



.....4 (ማቴ 28:19-20) ።

ይህንን ትእዛዝ የሰሙና አስፈላጊነቱን የተገነዘቡ ሐዋርያት ፤ ወደ እግዚአብሐር የመለሱአቸውን አማኞች መንፈሳዊ ሕይወታቸውን ይገነቡ እንደነበር በሐዋርያት ሥራ 2:41:-42 ተጽፎ እናገኛለን ። “ከነርሱ ብዙዎቹ ቃሉን ተቀብለው ተጠመቁ ፤ በዚያን ቀን ሶስት ሺህ የሚያህሉ አማኞች ተጨመሩ ። እነርሱም የሐዋርያትን ትምህርት በመስማት በወንድማማችነት አብሮ በመኖር ፤ እንጀራ በመቁረስና በጸሎት ይተጉ ነበር 3 ።

ሐዋርያ ጳውሎስ በኤፌ 4:11-13 ይህን አሳብ ጥርት አድርጎ አስፍሮታል ። በኤፌ 4:11 “ እርሱም [ ክርስቶስ ] አንዳንዶቹ ሐዋርያት ፤ አንዳንዶቹ ነቢያት ፤ አንዳንዶቹ የወንጌል ሰባኪዎች ፤ አንዳንዶቹ የምእመናን እረኞች ፤ አንዳንዶቹ አስተማሪዎች እንዲሆኑ ስጦታዎችን ሰጠ ” ይላል ። ይህም ማለት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋዮችን ለቤተ ክርስቲያን ሰጠ ማለት ነው ። ቀጥሎም በኤፌ 4:12-13 :- እነዚህን አገልጋዮች ለቤተ ክርስቲያን የሰጠበትን ምክንያት ይገልጣል ። ምክንያቱም ወደ ጌታ የተመለሱትን ምእመናን መንፈሳዊ ሕይወት እንዲገነቡና ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ መምሰል ደረጃ እንዲደርሱ ነው ።

“ይህንንም ያደረገው የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን እንድትታነጽ ....ነው ። ” (ኤፌ 4:12) ።

ይህ የማነጽ ወይም የማሳደግ አገልግሎት የማያቋርጥ ሥራ ነው ። ምክንያቱም ሰው በመንፈሳዊ ሕይወቱ አድጎ የሚያበቃበት ጊዜ የለም ። እድሜ ልኩን መማር መታነጽ መሠራትና መስተካከል ይኖርበታል ።

የማነጹ አላማ ምእመናን በመንፈሳዊ ሕይወታችን ክርስቶስን እንድንመስል ነው ። በኤፌ 4:13 እንዲህ ሲል ይህን አሳብ ይገልጣል ፤ " እንዲሁም የእግዚአብሔርን ልጅ በማወቅ በእምነት ወደሚገኘው አንድነት ደርሰን ፥ ክርስቶስ ፍጹምና ሙሉ እንደሆነው እኛም ሙሉ ሰው እንድንሆን ነው ። "

እግዚአብሔር ለልጆቹ ያለው ዘላለማዊ እቅዱ ፥ ክርስቲያኖች በጠባያቸውና በኑሮአቸው ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲመስሉ ነው ። ሐዋርያ ጳውሎስ ይህን ትምህርት በሮሜ 8:29 እንዲህ ሲል ይገልጣል ፥ " ....የእግዚአብሔር ልጅ በብዙ ወንድሞች መካከል በኩር እንዲሆን ፥ እግዚአብሔር አስቀድሞ የመረጣቸውን የልጁን መልክ እንዲመስሉ ስለወሰነ ነው ። "

"የልጁን መልክ እንዲመስሉ " ሲል ምን ማለቱ ነው ? የልጁን መልክ የምንመስለው በቀለም አይደለም ። በመልክ /በገጽታ አይደለም ። በቁመት አይደለም ። በጾታ አይደለም ። የልጁን መልክ የምንመስለው በመንፈሳዊ ሕይወት ነው ።

አመለካከታችን የክርስቶስን አመለካከት ምኞታችን የክርስቶስን ምኞት ፥ ተግባራችን የክርስቶስን ተግባር ፥ ኑሮአችን የክርስቶስን ኑሮ መምሰል አለበት ማለት ነው ። ይህን የክርስቶስ መልክ ለመምሰል የምንችለው በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ስንታነጽ ነው ። እርግጥ ነው ደህንነት ከዚህ መቅደም አለበት ። የተለወጠ ሕይወት ብቻ ነው ለመታነጽ የሚችለው ።

ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር ስለ መመለስና የምእመናንን



መንፈሳዊ ሕይወት ስለ ማነጽ ሲናገሩ አንዳንድ ሰዎች ሁለት የተሳሳቱ አመለካከትን ያንጸባርቃሉ ። አንዱ የተሳሳተ አመለካከት ቁጥር ላይ ብቻ ያተኩራል ። ይህም ማለት :- የቤተ ክርስቲያን ሐላፊነት ሰዎችን በብዛት ወደ ጌታ መመለስ ብቻ እንደሆነ አስመስለው ይናገራሉ ።

ሌላው የተሳሳተ አመለካከት ደግሞ ጥራት ላይ ብቻ የሚያተኩር ነው ። እንዲህ ያለ አመለካከት ያላቸው ሰዎች ፥ የቤተ ክርስቲያን ሐላፊነት የምእመናንን መንፈሳዊ ሕይወት ማነጽ ፥ መገንባትና ማሳደግ ብቻ እንደሆነ አስመስለው ይናገራሉ ።

በሁለቱም አመለካከት ውስጥ እውነት አለባቸው ። ነገር ግን ግማሽ እውነት እንጂ የተሟላ እውነት አይደለም ። ጌታ ለቤተ ክርስቲያን ተልእኮ ሲሰጥ እንዲህ ሲል ተናግሮአል ፥ " እንግዲህ ሂዱና የዓለምን ሕዝብ ሁሉ አስተምሩ ፤ በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁአቸው ። ያዘዝኋችሁን ሁሉ እንዲፈጽሙ አድርጉአቸው ....." (ማቴ 28:19-20) ።

በዚህ ትእዛዝ ውስጥ ሁለቱም አሳቦች ፥ ማለትም የቁጥሩም ጉዳይ ፥ የጥራቱም ጉዳይ ተጠቅሰዋል ። "የዓለምን ሕዝብ ሁሉ " የሚለው ቃል የቁጥር ብዛት ያመለክታል ። " አስተምሩ ...ያዘዝኋችሁን ሁሉ እንዲፈጽሙ አድርጉአቸው " የሚለው አሳብ የሕይወትን ጥራት ወይም እድገትን ያሳያል ። ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ የቁጥር ብዛትንም ፥ የሕይወት ጥራትንም የያዘ ነው ።

ይህን ተልእኮ በግልጥ የተረዱት ሐዋርያት በቁጥር ብዛትም ላይ በሕይወት ጥራትም ላይ እንዳተኮሩ ለመረዳት ይቻላል ።

በሐዋ.ሥራ 2:41 " ከእነርሱም ብዙዎቹ ቃሉን ተቀብለው ተጠመቁ ፤ በዚያን ቀን ሶስት ሺህ የሚያህሉ አማኞች ተጨመሩ " ይላል።

በሐዋ .ሥራ 4:4 :- " ነገር ግን ቃላቸውን ከሰሙት ሰዎች ብዙዎች አመኑ ፤ የአመኑትም ሰዎች ቁጥር ወደ አምስት ሺህ ከፍ አለ " ሲል የቁጥር ብዛትም የእግዚአብሔር እቅድ መሆኑን በግልፁ ያሳያል ። የቁጥሩም ብዛት የጌታ ፈቃድ መሆኑን የበለጠ ለማስረዳት አንድ መረጃ ለመጨመር እፈልጋለሁ ።

በሐዋ .ሥራ 5:14 :- " በጌታ የሚያምኑ ወንዶችና ሴቶች ቁጥራቸዉ በጣም እየበዛ ይሄድ ነበር " በማለት የአማኞች የቁጥር ብዛት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እቅድ መሆኑን በድጋሚ ያስገነዝበናል ።

ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው የቁጥር ብዛት የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሆነ ሁሉ የሕይወት ጥራት ፤ እድገትና ክርስቶስን የመምሰል ጉዳይም የግዚአብሔር ፈቃድ እንደሆነ በብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ተጠቅሰው እናገኛለን ።

ለምሳሌ :-በሐዋ.ሥራ 2:42 ተጽፎ እንደምናገኘው ፥ ሐዋርያት በብዛት ወደ ጌታ የተመለሱትን ምእመናን በእግዚአብሔር ቃል ሲያንጹአቸውና በፀሎት ሲያተጓቸው እናያለን ። የሐዋ.ሥራ 2:41 የቁጥርን ብዛት ያሳያል ። የሐዋ.ሥራ 2:42 የመንፈሳዊ ሕይወትን ጥራት ፥ እድገትና መጎልመስን ያሳያል ።

የሕይወት እድገት /ጥራት በአስተሳሰባችን ፥ በአመለካከታችን ፥ በፍላጎታችን ፥ በአኗኗራችን ሁሉ ክርስቶስን እንድንመስል ያደርገናል ። በእግዚአብሔር ትምህርት መታነጽ የእውነትን መንገድ



ትተን በዓለም ፍልስፍና በሐሰት ትምህርት እንዳንመራ ያደርገናል ። ሐዋርያ ጳውሎስ ይህን ጉዳይ ሲገልጥ እንዲህ ይላል ፥ " ከእንግዲህ ወዲህ በሰዎች ሽንገላና በአታላይነት ተንኮል በተዘጋጀ በአሳሳች የትምህርት ነፋስ ወዲያና ወዲህ እንደሚወሰዱ ሕፃናት አንሆንም " (ኤፌ 4:14) ።

ሐዋርያው ጳውሎስ መልእክቱን ለጢሞቴዎስ የጻፈበትን ዋና አላማ ከዚህ እንደሚከተለው ይገለጻል ፤ " ይህን መልእክት ስጽፍልህ በፍጥነት ወደ አንተ መጥቼ እንደማይህ ተስፋ በማድረግ ነው ። ብዘገይም በእግዚአብሔር ቤተሰብ መካከል ፥ ሰዎች እንዴት መኖር እንደሚገባቸው እንድታውቅ ጽፌልሃለሁ ። ይህም ቤተሰብ የእውነት አምድና መሠረት የሆነው የህያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ነው "(1ኛ ጢሞ 3;14:15) ።

ከዚህ በላይ በተጠቀሰው መልእክት ውስጥ እንደምንመለከተው ፥ አማኞች በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ሲኖሩና ሲያገለግሉ ፥ እንዴት መኖርና ማገልገል እንዳለባቸው ማወቅ አስፈላጊ ነው ። ይህን ማስተማር የቤተ ክርስቲያን ሐላፊነት ነው ።

ቤተ ክርስቲያን አማኞችዋን በእግዚአብሔር ላይ የተመሠረተ ፥ መሠረታዊና የጠራ ትምህርት ማስተማር ካልቻለች አማኞች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ሊያድጉና ሊታነጹ አይችሉም ።

ከዚህ የተነሳ አንዳንድ አማኞች በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ እንደ መንፈሳውያን የእግዚአባሐር ልጆች መመላለስን ትተው ፥ ለእግዚአብሔር አገልጋዮችና ለእግዚአብሔር ጉባኤ ችግር ፈጣሪዎችና ልብ አቁሳዮች ይሆናሉ ።

የእግዚአብሔርን ቃል ካለማወቃቸውና እንደ ቃሉም ካለመኖራቸው የተነሳ በትዳር ጓደኛ ምርጫ ስህተት ላይ ይወድቃሉ ። በእግዚአብሔር ቃል ላይ ለተመሠረተው የእግዚአብሔር ቤት አመራርና አሠራር ራሳቸውን ማስገዛት ይቸግራቸዋል ።

ስለ ትዳራቸው ፣ ስለ መንፈሳዊ ሕይወታቸው ፣ ስለ አገልግሎታቸውና ስለ ጠቅላላ ኑሮአቸው እንደ እግዚአብሔር ቃል ምክር ሲሰጣቸው ምክሩን በትህትና ተቀብለው ለእግዚአብሔር መኖር ያስቸግራቸዋል ።

መሠረታዊና ጥራት ያለው የእግዚአብሔር ቃል እውቀት ስለሌላቸው ፣ እግዚአብሔር በሰጣቸው የጸጋ ስጦታዎች ስህተትን በመሥራት ሌሎችንም ምእመናን ስህተት ላይ ይጥላሉ ። " የእግዚአብሔር ቃል ምን ይላል ?" እያሉ በእግዚአብሔር ቃል ከመመራት ይልቅ በራሳቸው ስሜትና ፍላጎት ፣ በእግዚአብሔር ቃል እውቀት ባልበሰሉ ሰዎች ምክር ይመራሉ ።

ይህም ወደ ተሳሳተ ትምህርት ፣ ወደ ተሳሳተ የኑሮና የአገልግሎት ምርጫ ያደርሳል ። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን አማኞችዋን በእግዚአብሔር ቃል መኮትኮት ፣ ማረምና ማሳደግ አለባት ። የእግዚአብሔርን ቃል /አሳብ ያለማወቅ ስህተት ላይ እንደሚጥል ሲገልጽ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ብሎ ተናገረ ፤ " እናንተ ቅዱሳት መጽሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል ባለማወቃችሁ ትስታላችሁ " (ማቴ 22:29) ።

ቤተ ክርስቲያን አማኞችዋን በገንዘባቸው ፣ በአገልግሎታቸው ፣ በጊዜያቸው ፣ እንዲሁም እግዚአብሔር በሰጣቸው መልካም ነገሮች ሁሉ ታማኝ መሆን እንዳለባቸው ካላስተማረች ምእመናን



በታማኝነት ለእግዚአብሔር ለመኖር አይችሉም ።

ክርስቲያኖች በሕይወታቸውና በአገልግሎታቸው ምሳሌነት ያለው ሕይወት እንዲኖራቸው ከተፈለገ ቤተ ክርስቲያን ጥራት ያለዉና መሠረታዊ ትምህርት ያለ ማቋረጥ ማስተማር አለባት።

" ነገር ግን የጠራችሁ እግዚአብሔር ቅዱስ እንደሆነ እናንተም በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ ። " (1ጴጥ 1:15) እያለች ቤተ ክርስቲያን ምእመናን በቅድስና የተሞላ ሕይወት እንዲኖሩ ማስተማር ማሳሰብና ደግማና ደጋግማ ማስታወስ አለባት ።

በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ የአመጽን ፣ የመለያየትን ፣ የመከፋፈልን ፣ የአድመኝነትንና የብጥብጥን ዘር የሚዘሩ ሰዎች ሕይወታቸው በእግዚአብሔር ቃል ስላልተሰበረና ስላልተለወጠ ነው ። ስለዚህ ሕይወታቸው በእግዚአብሔር ቃል ተሰብሮ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር እንዲያስገዙ ፣ የአመጽ መሳሪያዎች ከመሆን ይልቅ የጽድቅ መሳሪያዎች እንዲሆኑ ፣ የመከፋፈል መሳሪያዎች ከመሆን ይልቅ የአንድነትና የሕብረት መሳሪያዎች እንዲሆኑ ያለመሰልቸት ማስተማር አስፈላጊ ነው ።

ይህ የምንኖርበት ዘመን እምነትን የሚያናጉ ፣ ትዳርን የሚያቃዉሱ ፣ ሕብረትን የሚያፈራርሱ ፣ ሰይጣን የምጠቀምባቸው ልዩ ልዩ ፍልስፍናዎችና ልማዶች እንደ ነፋስ የሚነፍሱበት ዘመን ነው ። ይህ ዘመን አመጽ ፣ ራስ ወዳድነት ፣ ትእቢት የሞላበት ዘመን ነው ። ሰዎች ከሕያው እግዚአብሔር አሳብና አሠራር ይልቅ የሰውን አሳብና አሠራር የሚመርጡበት ዘመን ሆኖአል።

ከዘመኑ ሰዎች አሳብና አሠራር ጋር እንዲስማማ ፣ የእግዚአብሔርን

ቃል እንኳ ለማሻሻልና ለመለወጥ ድፍረት የሚደረግበት ዘመን ሆኖአል ። የእግዚአብሔር ቃል ዘመናትን ፥ ሰማይንና ምድርን ሁሉ አሳልፎ ለዘላለም የሚኖር ነው ።

ቤተ ክርስቲያን ይህን እውነት ድምጿን ከፍ በማድረግ ለምእመናን ማስተማር አለባት ። ቤተ ክርስቲያን ለእግዚአብሔር ቃል ታማኝ መሆን አለባት ። ቀይ ሽንኩርትን እስከ መጨረሻው ቢልጡት ጨርሶ ያልቃል ። ቀሪ ነገር አይኖረውም ። ስለዚህ ሽንኩርት የምትልጥ ሴት ሽንኩርቱ ተልጦ እንዳያልቅባት ትጠነቀቃለች።

በየዘመኑ ከሚመጣው የሰዎች ፍልስፍና አመለካከት ጋር ለመስማማት ሲሉ የእግዚአብሔርን ቃል /በየጊዜው ትንሽ በትንሹ ሲልጡት ከዚህ በላይ እንደጠቀስሁት ቀይ ሽንኩርት የእግዚአብሔር ቃል ያለቀባቸው ቤተ ክርስቲያኖች በዓለማችን አሉ ።

ሌሎች ደግሞ ከዚህ በላይ ያለውን ፍላጎት ለማሟላት ሲሉ ንጹሑን የእግዚአብሔር ቃል / አሳብ እየበረዙ እንደ አገራችን የጠላ ቅራሪ ወይም እንደ ሶስተኛ ቡና መለኮታዊ ጣዕሙን እንዲያጣ ያደረጉ ቤተ ክርስቲያኖች አሉ ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ቃሉን እንዴት መጠበቅና ማስተማር እንዳለባት ሲያስተምር ከዚህ እንደሚከተለው ተናገረ ፤ “ ከእነዚህ ትእዛዛት አነስተኛ የሆነችውን አንዷን እንኳ የሚያፈርስና ሌሎችም ሰዎች እንዲህ እንዲያደርጉ የሚያስተምር ሰው በመንግሥተ ሰማይ አነስተኛ / ታናሽ ይሆናል ። ነገር ግን ትእዛዛትን ሁሉ የሚፈጽምና ሌሎችም ሰዎች እንዲሁ እንዲፈጽሙ የሚያስተምር ሰው በመንግስተ ሰማይ ታላቅ ይሆናል ” (ማቴ 5:19) ።



ከታሪክ አምዶች እንደምናነበው አንድ ትውልድ እንደ ሕያው አሳብ ወይም እውነት የተቀበለውን ፥ ያወጀውን ፍልስፍና የሚቀጥለው ትውልድ እንደ ቤት ጥራጊ ሲጥለው አይተናል ። የሰው የዘመኑ ፍልስፍና ቀርቶ ሰማይና ምድር እንኳ ያልፋል ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ “ ሰማይና ምድር ያልፋሉ ፤ ቃሌ ግን ለዘላለም ይኖራል ” (ማቴ 24:35) ሲል ተናግሮአል ።

በሐዋርያት ዘመን የእግዚአብሔርን ቃል የሚሸቃቅጡ አገልጋዮች ነን የሚሉ ሰዎች ነበሩ ። ሐዋርያ ጳዉሎስ ግን ራሱንም ለእግዚአብሔር ቃልና አሠራር እያስገዛ ሌሎችም እንዲሁ ራሳቸዉን ለሕያው እግዚአብሔር ቃልና አሳብ እንዲያስገዙ ፥ እንደ ዘመኑ ፍልስፍና ሳይሆን እንደ እግዚአብሔር አሳብ እንዲኖሩ ያስተምር ነበር ።

ስለዚህ ጉዳይ እንዲህ ሲል ይገልጻል ፤ “እኛ እኮ የእግዚአብሔርን ቃል እንደ ንግድ እቃ እንደሚቸረችሩት እንደ ብዙዎቹ አይደለንም ፤ ነገር ግን ከእግዚአብሔር የተላከን የክርስቶስ አገልጋዮች ሆነን በእግዚአብሔር ፊት በቅንነት እንናገራለን ” (2ቆሮ 2:17) ።

አማኞችን በመከራ ጊዜ ደግፎ የሚያቆማቸው ፥ እንደ ነፋስ በሚነፍሰው የዘመኑ የሰዎች ፍልስፍና እንዳይናወጡና እንዳይወሰዱ የሚያደርጋቸው ነገር ቢኖር በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረተ መሠረታዊና የጠራ ትምህርት ነው ።

የቃሉ አገልግሎት አማኞችን ለጊዜው ሞቅ የሚያደርግ ፥ ለጊዜው አስጨብጭቦና እልል አሰኝቶ የሚያሰናብት ብቻ መሆን የለበትም ። የልብ ግለት ፥ ለእግዚአብሔር ማጨብጨብና እልል

ማለት ስህተት ነው ማለቴ አይደለም ።

ቤተ ክርስቲያን ለምእመናኗ የምትሠጠው የቃሉ አገልግሎት ለጥቂት ደቂቃዎች ብቻ ሙቀትን እንደሚሰጥ የገለባ እሳት መሆን የለበትም ። ይልቁንም ብረትን እንደሚያግል የከሰል እሳት ውስጣዊ ሰውነትን የሚያቃጥል ፣ ስብሰባ ከተበተነ በኋላ እንኳ ምእመናን " እርስ በርሳቸው ......ሲናገረን ፣ መጻሕፍትንም ሲከፍትልን ልባችን ይቃጠልብን አልነበረምን ? " (ሉቃ 24:3) የሚያሰኝ የጠራና መሠረታዊ ትምህርት ማስተማር አስፈላጊ ነው ።

በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረተ ፣ የጠራና መሠረታዊ የሆነ ትምህርት አማኞች በመከራም ጊዜ እንኳ ቢሆን ልባቸው በእምነትና በተስፋ እንዲግል ፣ እጆቻቸው ለእግዚአብሔር ክብር እንዲያጨበጭቡና እንደበታቸው ለስሙ ምስጋና እልል እንዲሉ ያደርጋል ።

የመድረክ አገልግሎት በእግዚአብሔር ቃልና በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ መሆን አለበት ። የእግዚአብሔር ቃልና መንፈስ ቅዱስ መታየት ያለባቸው እንደ ሁለቱ የአሞራ ክንፎች መሆን አለበት ። አሞራ የሰውነቷን ሚዛን ጠብቃ በአየር ላይ ለመብረር ከፈለገች ሁለቱም ክንፎችዋ ጤነኛና የሚሠሩ መሆን አለባቸው ። ይህ ካልሆነ ግን አሞራዋ ወድቃ ትከሰከሳለች ።

ስለዚህ የአገልግሎታችን መድረክ በእግዚአብሔር ቃልና በእግዚአብሔር መንፈስ ሚዛኑን የጠበቀ መሆን አለበት ። ይህም ማለት በአንድ ነገር ላይ ብቻ ማተኮር ሳይሆን ጠቅላላውን የእግዚአብሔርን አሳብ ለምእመናን ማስተማር አስፈላጊ ነው ።



ስለዚህ ጉዳይ የሐዋርያ ጳውሎስን አገልግሎት መመልከት ጠቃሚ ነው ። ጳውሎስ በአንድ ነገር ላይ ብቻ ማተኮር ሳይሆን ጠቅላላውን የእግዚአብሔርን አሳብ ያስተምር እንደ ነበር ከዚህ እንደሚከተለው ይገልጻል ፤ " በአደባባይም ሆነ በቤታችሁ ሳስተምራችሁ የሚጠቅማችሁን ሁሉ ነገርሁአችሁ እንጂ ምንም ነገር አላስቀረሁባችሁም " (የሐዋ 20:20) ።

ስለዚህ ጳውሎስ የኤፌሶንን ምእመናን ለመጨረሻ ጊዜ ሲለያቸው ከዚህ ቀጥሎ ባለው ሁኔታ በድፍረት ለመናገር ችሏል ። " ስለዚህ ከእናንተ አንድ እንኳ ቢጠፋ ኃላፊነት እንደሌለብኝ በዛሬው ቀን አስገነዝባችኋለሁ ። ምክንያቱም የእግዚአብሔርን አሳብ ሁሉ ነገርሁአችሁ እንጂ ምንም ያስቀረሁባችሁ ነገር የለም " (የሐ.ሥ 20:20-27) ።

እንደዚህ ዓይነቱ የተሟላና ሁሉን አጠቃላይ የሆነ የቃሉ አገልግሎትና ትምህርት ምእመናንን ያንጻል ፣ በመከራ ጊዜ በእምነት ያቆማቸዋል ፣ በቅድስና እንዲኖሩ ያደርጋቸዋል ፣ ከስህተት ትምህርት ይጠብቃቸዋል ፣ ለእግዚአብሔርም መንግሥት ያበቃቸዋል ።

በዚህ ምክንያት ነው ሐዋርያ ጳውሎስ እንዲህ ሲል ለመናገር የቻለው ፤ "አሁንም ለእግዚአብሔር ፣ ሊያንጻችሁና በቅዱሳንም መካከል ርስት ሊሰጣችሁ ለሚችለው ለጸጋው ቃልም አደራ ሰጥቻችኋለሁ " (የሐ.ሥ 20:32) ።

ምእመናንን ማነጽ እንክብካቤንም ይጨምራል ። የምእመናንን መንፈሳዊ ሕይወት ማነጽ ለምእመናን እንክብካቤና ጥበቃ ማድረግንም ይጨምራል ። እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚያስብና የሚጠነቀቅ

አምላክ ነው ። ከዚህ የተነሳ ለሕዝቡ እንክብካቤ ማድረግን የዘነጉትን የእስራኤልን አገልጋዮች ከዚህ እንደሚከተለው ወቀሳቸው ። " ለደከሙት እንክብካቤ አላደረጋችሁላቸውም ፤ የታመሙትን አላዳናችሁም ፤ የተሰበሩትን አልጠገናችሁም ፤ የባዘኑትን አልመለሳችሁም ፤ የጠፉትን አልፈለጋችሁም ....." (ሕዝ 34:4) ።

ይህ ዓለም መከራ የሞላበት ዓለም ነው ፤ አማኝም ቢሆን በዚህ ዓለም መከራ ውስጥ ያልፋል ። እግዚአብሔርን በማይከተሉ ሕዝብና የሕዝብ መሪዎች ምክንያት የሚመጡት የፖለቲካ ፣ የኢኮኖሚ ፣ የሕብረተሰብ ችግሮች የአማኞችንም ሕይወትና ኑሮ ይነካሉ ።

በአንድ አገር ላይ የሚደርሱ የዝናብ እጦት ፣ የመሬት መናወጥ ፣ የእሳት አደጋና የጎርፍ ማጥለቅለቅ በዚያ አገር የሚኖሩትን አማኞች ኑሮ መንካቱ አይቀርም ። በአንድ አገር የሃይማኖት ስደት ሲነሳ አማኞች የመከራን ጽዋ ይካፈላሉ ።

እግዚአብሔር ግን የራሱን ሕዝብ የሚታደግ ታማኝና ርሕሩህ አምላክ ነው ። በግብጽ ምድር በሕዝቡ ላይ የደረሰውን መከራና ስቃይ እግዚአብሔር ከዚህ በሚከተለው ሁኔታ ይገልጸዋል ፤ "ሕዝቤ በግብጽ ምድር በምን ዓይነት ስቃይና መከራ ላይ እንዳሉ አይቻለሁ ፤ ከአስጨናቂዎቻቸው የሚታደጋቸውን በመፈለግ የሚያሰሙትን ጩኸት ሰምቻለሁ ። የደረሰባቸውን መከራ አውቃለሁ ። እነርሱንም ከግብጻውያን እጅ ለመታደግ እወርዳለሁ ......" (ዘጸ 3:7-8) ።

በመከራም ጊዜ እንኳ እግዚአብሔር ከሕዝቡ እንደማይለይ በቃሉ ተጽፎ እናገኛለን ። "በጥልቅ ውሃ ውስጥ በምታልፍበት



ጊዜ ከአንተ ጋር እሆናለሁ ፤ የመከራ ብዛት አያሰጥምህም ፤ በእሳትም ውስጥ በምታልፍበት ጊዜ አያቃጥልህም ፤ የሚደርስብህም ፈተና አይጎዳህም " ( ኢሳ 43:2 ) ።

እነዚህ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ጥቅሶች አማኞች በመከራ ውስጥ እንዳለፉና ወደፊትም እንደሚያልፉ ያሳያሉ ። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደማይተው የተረጋገጠ ጉዳይ ነው ።

በመከራ ውስጥ የሚያልፈው የእግዚአብሔር ሕዝብና እያንዳንዱ አማኝ እንክብካቤና መጽናናት ያስፈልጋቸዋል ። ለዚህ ነው እግዚአብሔር የሕዝቡን አገልጋዮች እንዲህ ሲል ያዘዛቸው ፤ " አጽናኑ ፣ ሕዝቤን አጽናኑ " ( ኢሳ 40:1 ) ።

የብሉይ ኪዳን ምእመናን ብቻ ሳይሆኑ የአዲስ ኪዳን ምእመናንም ቢሆኑ ይህች ዓለም በምታፈራው መከራ ውስጥ ያልፋሉ ። ይህ እንደሚሆን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግልጽ አድርጎ ለተከታዮቹ አስገንዝቦአል ። " በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ ....." ( ዮሐ 16:33 ) ።

ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን በልዩ ልዩ ችግሮች ውስጥ የሚያልፉትን በክርስቶስ ፍቅርና ርህራሄ ማጽናናት ይኖርባታል ። ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስ በዚህ ዓለም በነበረበት ጊዜ ያሳየውን መለኮታዊ ባህሪይ ለምታገለግላቸው ምእመናን ማሳየት አለባት ።

የተሰበሩትን ለመጠገን ፣ ያዘኑትን ለማጽናናት ፣ ተስፋ ለቆረጡት የተስፋን ቃል ለማሰማት ፣ ብቸኝነት ላጠቃቸው ወዳጅ /ጓደኛ ለመሆን ፣ የወደቁትን ለማንሳት ፣ የሚንገዳገዱትን ለመደገፍ

፣ የጠፉትን ለመፈለግ ፣ ያጡትን ለመርዳት የኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅርና ርህራሄ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሙላት መሥራት ያስፈልጋል።

እስቲ ኢየሱስ ክርስቶስ ላገለገላቸው ሰዎች ያሳያቸውን መለኮታዊ ባህሪያት አለፍ አለፍ እያልን እንመልከት ።

“ እንዲሁም ኢየሱስ በምኩራቦቻቸው እያስተማረ ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት መልካም ዜና እያበሰረ ፣ ሕዝቡን ከበሽታና ከደዌ ሁሉ እየፈወሰ ፣ በከተማዎችና በመንደሮች ሁሉ ይዘዋወር ነበር ። ሕዝቡ እረኛ እንደሌላቸው በጎች ተጨንቀውና ረዳት አጥተው ባያቸው ጊዜ ራራላቸው ” ( ማቴ 9:35-36 )።

“ ኢየሱስም ከጀልባው በወረደ ጊዜ ብዙ ሰዎችን አይቶ ራራላቸው ፤ በሽተኞቻቸውንም ፈወሰላቸው ። በመሸም ጊዜ ደቀመዛሙርቱ ወደ እርሱ ቀርበው ፣ ይህ ቦታ በረሃ ነው ፤ ቀኑም መሽቶአል ፤ ሕዝቡንም በአቅራቢያ ወዳሉት መንደሮች ሄደው ምግባቸውን እንዲገዙ አሰናብታቸው አሉት ። ኢየሱስ ግን እናንተ የሚበሉትን ስጡአቸው እንጂ እነርሱ እንዲሁ ሊሄዱ አይገባም አላቸው ” ( ማቴ 14:14-16 ) ።

“ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ጠርቶ እንዲህ አላቸው ፣ ሕዝቡ ከእኔ ጋር ሶስት ቀናቸው ስለሆነና የሚበሉት ስለሌላቸው እራራላቸዋለሁ ፤ ሲሄዱ በመንገድ ዝለው እንዳይወድቁ ምንም ሳይመገቡ ላሰናብታቸው አልፈቅድም ” ( ማቴ 15:32 ) ።

“ እነርሱ ግን የዳዊት ልጅ የሆንህ ጌታ ሆይ ! እባክህ ማረን እያሉ አብዝተው ጮኹ ። ኢየሱስም ቆሞ ጠራቸውና ምን እንዳደርግላችሁ ትፈልጋላችሁ አላቸው ። እነርሱም ጌታ



ሆይ ! ዐይኖቻችን እንዲከፈቱ እንፈልጋለን አሉት ። ኢየሱስም ራራላቸውና ዐይኖቻቸውን ዳሰሰ ፤ ወዲያዉኑ ዐይኖቻቸው ተከፈቱ ፤ ኢየሱስንም ተከትሉት ” ( ማቴ 20:31-34 ) ።

“ አንድ ለምጻም ወደ ኢየሱስ መጣና በእግሩ ስር ተንበርክኮ ብትፈቅድስ ልታነጻኝ ትችላለህ ሲል ለመነው ። ኢየሱስም ራራለትና እጁን ዘርግቶ እየዳሰሰው እፈቅዳለሁ ፣ ንጻ አለው ። ሰውየውም ከለምጹ ወዲያዉኑ ነጻ ” ( ማር 1:40-42 ) ።

ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ጥቅሶች እንደምንመለከተው ፤

1ኛ/-ኢየሱስ ክርስቶስ በርህራሄ የተሞላ ጌታ ነበር ። አሁንም ነው ። የመለኮቱ ባህርይ ተከዮች የሆን አገልጋዮች / ተከታዮች ሁሉ በርህራሄ የተሞላን ሰዎች መሆን አለብን ።

2ኛ/-ለሰዎች ያደረገላቸዉን በጎ ነገሮች ሁሉ እንዲያደርግላቸው የገፋፋው ለሰዎች የነበርው ርህራሄው ነው ። መለኮታዊ ርህራሄ ነው የገፋፋው ። መለኮታዊ ርህራሄ ነው ያበረከተውን አገልግሎት እንዲያበረክት ያደረገው ።

በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ለተቀደሰው የወንጌል አገልግሎት የተጠሩና ከመንፈስ ቅዱስ ጸጋን የተቀበሉ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ሁሉ የእግዚአብሔርን ሕዝብ በርህራሄ ማገልገል ይገባቸዋል / ይገባናል ።

ለምእመናኗ እንክብካቤ የማታደርግ ቤተ ክርስቲያን ፣ ልጆችን ወልዳ ልጆችዋን በፍቅርና በርህራሄ እየተንከባከበች የማታሳድግን እናት ትመስላለች ።

የማጽናናት አገልግሎት በእውነተኛ ፍቅርና ርህራሄ የትቀመመ መሆን አለበት ። በእውነተኛ ፍቅርና ርህራሄ የሚሰጥ አገልግሎት ፥ የተሰበረውን ሕይወት ይጠግናል ፤ የቆሰለውን ሕይወት ይፈውሳል ፤ ያዘነውን ልብ በደስታ ይሞላል ፤ የወደቀውን ያነሳል ፤ የተንገዳገደውን ይደግፋል / ያቆማል ፤ የጠፋውን ፈልጎ ያመጣል ፥ ተስፋ ለቆረጠ ተስፋን ይሰጣል ።

የማጽናናት አገልግሎት ከቤተ ክርስቲያን መድረክ ብቻ የሚሰጥ መሆን የለበትም ። የምእመናን እንክብካቤ ከቤተ ክርስቲያን መድረክም ፥ ሲያስፈልግ ደግሞ በምእመናንም ቤት መሰጠት አለበት ።

ሐዋርያው ጳውሎስ ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ምእመናንና አገልጋዮች የሰጣቸው አገልግሎት የተሟላ አገልግሎት እንደ ነበር ራሱ ገልጦታል ። “ በአይሁዳውያን ሴራ ምክንያት መከራ ቢደርስብኝም እንኳ በፍጹም ትህትናና በእንባ ጌታን አገልግያለሁ ። በአደባባይም ሆነ በቤታችሁ የሚጠቅማችሁን ሁሉ ነገርሁአችሁ እንጂ ምንም ነገር አላስቀረሁባችሁም ” ( የሐ.ዋ 20:19-20 ) ።

በተጨማሪም ይህን አሳብ ሲገልጽ ጳውሎስ እንዲህ ይላል ፤ “ ስለዚህ እያንዳንዳችሁን ሶስት ዓመት ሌሊትና ቀን እንባዬን እያፈስስሁ እንደመከርኩአችሁ እያስታወሳችሁ ተጠንቀቁ ” ( የሐ.ዋ 20:31 ) ።

ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ጥቅሶች እንደምንረዳው ከጳውሎስ የጉባኤ አገልግሎት ብዙ ጠቃሚና ወቅታዊ የሆኑ ምሳሌዎችን እንማራለን ። እስቲ እነዚህን ነጥቦች እንመልከት ።



፩ኛ/ ምእመናንን በጉባኤ / ከመድረክ ያስተምር ፥ ይመክርና ያጽናና ነበር ።

፪ኛ/ በጉባኤ /ከመድረክ ብቻ ሳይሆን እንደአስፈላጊነቱ በየቤታቸውም እየተዘዋወረ ያስተምር ፥ ይመክርና ያጽናና ነበር።

፫ኛ/ ጳውሎስ አገልግሎቱን የሰጠው በታማኝነት ፥ በትህትና ፥ በፍቅር ፥ በእንባና በርህራሄ ነበር ።

በትህትና ፥ በፍቅር ፥ በርህራሄና በእንባ የሚሰጥ የማጽናናትና የምክር አገልግሎት የወደቀውን ያነሳል ። የተሰበረውን ይጠግናል ። የቆሰለውን ይፈውሳል ። የራቀውን ያቀርባል ። ተስፋ የቆረጠውን በተስፋ ይሞላል ።

ለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን መለኮታዊ ምክር የሚሰጠን ። “ ቅዱሳንን በሚያስፈልጋቸው እርዱ ፥ እንግዶችን ለመቀበል ትጉ .... ደስ ከሚላቸው ጋር ደስ ይበላችሁ ፥ ከሚያለቅሱም ጋር አልቅሱ ” ( ሮሜ 12:13,15 ) ።

ርህራሄና ማጽናናት የእግዚአብሔር መለኮታዊ ባህርያት ናቸው ። ጳውሎስ ስለዚህ ጉዳይ ሲጽፍ እንዲህ ይላል ፤ “ የርህራሄ አባት ፥ የመጽናናትም አምላክ የሆነ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ ። እርሱ በመከራችን ሁሉ ያጽናናናል ፥ ስለዚህም እኛ ራሳችንን ከእግዚአብሔር በምንጽናናበት መጽናናት በመከራ ሁሉ ያሉትን ማጽናናት እንችላለን ” ( 2 ቆሮ 1:3-4 ) ።

ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ጥቅሶች ሶስት ነጥቦችን ለመጥቀስ እፈልጋለሁ ።

1ኛ/እግዚአብሔር ርህሩህ ነው ። ስለሆነም የርህራሄ ሁሉ ምንጭ ነው ። ከእግዚአብሔር የሚመነጨውና ከሰው የሚመጣው ርህራሄ አንድ አይደሉም ። እውነተኛ ርህራሄ ከእግዚአብሔር ባህሪይ የሚመነጭ ርህራሄ ነው ።

2ኛ/እግዚአብሔር ርህሩህ ከመሆኑ የተነሳ የልጆቹ ችግር / ሃዘን ልቡን ይነካዋል ። የልጆቹን ለቅሶ ይሰማል ። መከራቸውን ያያል ( ዘጸ 3:7 ) ።

3ኛ/እግዚአብሔር የልጆቹን ለቅሶ ሰምቶ ዝም አይልም ። መከራቸውን አይቶ ጸጥ አይልም ። እጆቹን ዘርግቶ ይታደጋቸዋል ። ይዳስሳቸዋል ። ድምጹን አሰምቶ ያጽናናል ። አይሰለችም ። “ በመከራችን ሁሉ ያጽናናናል ። ”

እኛ የእግዚአብሔር ልጆች የአምላካችንና የአባታችን የመለኮቱ ባህርይ ተካፋዮች ነን ( 2ጴጥ 1:4 ) ። ስለሆነም እንደ አምላካችንና እንደ አባታችን የማጽናናትና የርህራሄ ዕቃዎች / መሳሪያዎች መሆን አለብን ። ርህራሄን ለብሰን “ ከእግዚአብሔር በምንጽናናበት መጽናናት በመከራ ያሉትን ሁሉ ማጽናናትና መንከባከብ ይገባናል ” ( 2 ቆሮ 1:4 ) ።

ቤተ ክርስቲያን ለምእመናኗ እንክብካቤ ማድረግ ካልቻለች ተልእኮዋ የተጓደለ ፥ አገልግሎትዋ እንካሳ ይሆናሉ ። በተለይም አገልጋዮች ይህን ታላቅ ኃላፊነት መዘንጋት የለብንም ። እግዚአብሔር በማጽናናት ጸጋ የቀባቸውንም አሰልጥኖ ማሰለፍ የቤተ ክርስቲያን



ኃላፊነት ይሆናል ። ምእመናንን በጉባኤም ፥ በቤታቸውም ፥ በሆስፒታል የሚያጽናና አገልግሎት ከሌለ ፥ ከመድረክ ቃሉን በማስተማር ብቻ መንፈሳዊ ሕይወታቸውን ለማነጽ አይችልም።

እስከ አሁን ከቤተ ክርስቲያን ተልእኮ ሁለቱን ዋና ዋና ክፍሎች ተመልክተናል ። እነዚህም ፥ ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር መመለስና የተመለሱትን ምእመናን መንፈሳዊ ሕይወት በእግዚአብሔር ቃል ማነጽ ናቸው ። በሚቀጥለው ምዕራፍ ሦስተኛውን የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ ክፍል እንመለከታለን ። እርሱም ምእመናንን ለመንፈሳዊ አገልግሎት ማዘጋጀትና ማሰለፍ ነው ።